# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

እሁድ 84 ዓመት ቁጥር 040 ጥቅምት 10 ቀን 2017 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




# “በመጀመሪያው ሩብ ዓመት በተለያዩ ዘርፎች ላቅ ያሉ እድገቶች ተመዝግበዋል”

- ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር)

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- በመጀመሪያው ሩብ ዓመት በተለያዩ ዘርፎች ላቅ ያሉ እድገቶች መመዝገባቸውን ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ገለጹ።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ በማህበራዊ ትስስር ገጻቸው ትናንት ባስተላለፉት መልዕክት፤ የመጀመሪያ ሩብ ዓመት የ100 ቀን ግምገማችን በተለያዩ ዘርፎች ላቅ ያሉ እድገቶች መመዝገባቸውን አሳይቶናል ብለዋል።

ይሁንና የእድገት አቅጣጫችን ከፊታችን የበለጠ ሥራ እንደሚቀረን ያመለክተናል ያሉት ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ (ዶ/ር)፤ስንተገብራቸው የቆየነው የተቋም እና የሲቪል ሰርቪስ ለውጥ ሥራዎች የእድገት ጥረታችንን በመደገፍ ላይ ይገኛሉ ሲሉ ገልጸዋል።

የሕዝብ አገልግሎቱ ዘርፍ አዲሱን የማብቃት ባሕል እንዲያሳድግ እና ሌሎችም ውጤታማ እንዲሆኑ እንዲደግፍ እጠይቃለሁ ሲሉ ጥሪ አስተላልፈዋል።

የ2017 በጀት ዓመት የመጀመሪያው የ100 ቀናት አፈጻጸም ግምገማ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በተገኙበት ለሁለት ቀናት ተካሂዷል።

የፕላንና ልማት ሚኒስትሯ ፍጹም አሰፋ (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ በተያዘው በጀት ዓመት የ8 ነጥብ 4 በመቶ እድገት የማስመዝገብ ውጥን መያዙን ተናግረዋል።

በ2017 የመጀመሪያው 100 ቀናት ተግባራዊ የተደረገው የተሟላ የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው የተሻለ የኢኮኖሚ አፈጻጸም

“በመጀመሪያው ሩብ ... ወደ ገጽ 5 ዞሯል



## ታሞ ከመማቀቅ አስቀድሞ መመርመር

**ዮርዳኖስ ፍቅሩ**

**ዜና ሐተታ**

የሀገሬ ሰው “ዋናው ነገር ጤና” ይላል፣ እንደ ማኅበረሰብ ለጤናችን ቅድሚያ ሰጥተን፤ ህመም ፀንቶ ከመምጣቱ አስቀድመን ወደ ጤና ተቋም የማቅናት፣ ጤናችንንም የመመርመር ልምድ የለንም። ብዙዎቻችን ወደ ጤና ተቋም የምናመራው ህመም ሲፀናብን ሲገጥመን

ታሞ ከመማቀቅ... ወደ ገጽ 5 ዞሯል

## አደጋ የደቀነው የጥላቻ ንግግር እና ሐሰተኛ መረጃ ስርጭት

**ቃልኪዳን አሳዬ**

**ዜና ትንታኔ**

ዜጎች ሃሳባቸውን በነጻነት የመግለጽ ሙሉ መብት እንዳላቸው ሁሉ የሌሎችን መብትና ደህንነት ግምት ውስጥ ማስገባትና ማክበር እንዳለባቸው ዓለም አቀፍ ህጎች ይደነግጋሉ። ይሁን እንጂ የማህበራዊ ሚዲያ መስፋፋት ይህንን ጉዳይ ፈተና ውስጥ እየከተተው ነው። የጥላቻ ንግግርና የሀሰተኛ መረጃ ስርጭት የሀገርን ሰላም በማደፍረስ የዜጎችን ደህንነት አደጋ ላይ የሚጥል ሆኗል፤ ዜጎችን እርስ በርስ በማጋጨትና በመከፋፈል የሀገርን ሰላም እያደፈረሰ ነው።

ማህበራዊ ሚዲያን በኃላፊነት መጠቀም እንደሚገባ የዘርፉ ባለሙያዎች አፅንኦት ሰጥተው ይገልጻሉ። ለመሆኑ በኢትዮጵያ የጥላቻ ንግግርና የሐሰተኛ መረጃ

አደጋ የደቀነው... ወደ ገጽ 5 ዞሯል



## የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው የማዕድናት ምርታማነትን እያሳደገ ነው

**ታደሠ ብናልፈው**

አዲስ አበባ፡- ተግባራዊ እየተደረገ ያለው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ የወርቅ ምርትን በከፍተኛ መጠን እያሳደገ መሆኑን የማዕድን

የማክሮ ኢኮኖሚ ... ወደ ገጽ 5 ዞሯል
















# የሀገር አንድነትና ሰላም የሚያጸናው ምክክር

**ውብሸት ሰንደቁ**

**ዜና ሐተታ**

ጅግጅጋ የአንድነት ማኅተማችንን በምክክር እናፅና የሚለውን ክተት ለማስተናገድ ሽር ጉድ ብላ ተሳታፊዎች ተቀብላለች፡፡ብዕር ይዞ በአመክንዮ መሞገት፤ ሃሳብ አንስቶ በልዕልና መርታት ነው የምክክሩ ዓላማ።ይህም የኢትዮጵያን ልጆች ከግጭት እና ከንትርክ አዙሪት ይታደጋል ተብሎ የታመነበት ክተት ነው፡፡

ሀገራዊ ምክክር ሂደቱ በጣም ጥሩ እና ውጤቱም መልካም እንደሚሆን የሚጠበቅ ነው ይላሉ ከአዋሬ ወረዳ የተገኙት የማኅበረሰብ ተወካይ አቶቾቢን አሕመድ ሀሰን።

ከልብ ከተመካከርን የምክክር መድረኩ ጥሩ ውጤት ያመጣል ብለው እንደሚያምኑ የሚናገሩት የማኅበረሰብ ተወካዩ፤ ወንድማማቾች ሆይ እርስ በራሳችሁ ተጋገዙ እንጂ አትገዳደሉ ማለት እፈልጋለሁ ሲሉ ይመክራሉ፡፡

ጥላቻ እና ግጭት ሀገሪቱንም ሆነ ክልሎቹን ዋጋ እያስከፈለ መሆኑን በመጥቀስ፤ ችግሮች በግጭት የሚፈቱ ቢሆን ሶማሌ ክልል ከዚህ ቀደም የነበሩ ግጭቶች ሁሉ ቀድሞ መፍታት ይችል እንደነበር ያጣቅሳሉ።

ችግሮችን በግጭት መፍታት እንደማይቻል በማመን ክልሉ በአሁኑ ጊዜ ሰላማዊ ምክክሮችን ምርጫው እያደረገ መምጣቱን በመናገር፤ በግጭት ውስጥ ያሉ ክልሎች ከሶማሌ ክልል ሊማሩ ይገባል ይላሉ።

በግጭት ውስጥ ለሚገኙ ክልሎች “በጥላቻ እና በግጭት ወንድ ይሞታል እንጂ ወንድ አይወለድም” ማለት እፈልጋለሁ ሲሉ ያስረዳሉ፡፡

በግጭት ውስጥ ያሉ ክልሎች ሀገርን ሲያስተዳድሩ የነበሩ እና ጥሩ ልምድ ያላቸው መሆናቸውን በመጥቀስ፤ ችግሮችን በምክክር መፍታት ከእነዚህ ክልሎች የሚጠበቅ እንደሆነ ያስገነዝባሉ።

ሀገራዊ ምክክር በተለይ በክልሎች መካከል ያለውን ግጭት የሚፈታ እንደሚሆን እንደሚያምኑ በመግለጽ፤ ከዚያም አልፎ መንግሥት ዴሞክራሲያዊ ሥርዓትን እንዲከተል ያደርጋል።እያንዳንዱ ዜጋም በዜግነቱ ኮርቶ የሚኖር እንጂ የሌላ ሀገር ናፋቂ እንዳይሆን ዕድል ይፈጥራል በማለት ያስረዳሉ፡፡



**አቶ ቾቢን አሕመድ ሀሰን**



**አቶ አብዱሰላም መሐመድ**



**አቶ አሕመድ መሐመድ**

መንግሥት ከሀገራዊ ምክክሩ የሚመነጩትን ውጤቶች ተግባራዊ እንዲያደርግ አፅንዖት መስጠት እፈልጋለሁም ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

እኛ የሀገራዊ ምክክር ዘማቾች በሕዝብ ውክልና ሀገራችንን ለማፅናት እየታገልን እንገኛለን ያሉት ተወካዩ፤ ከውስጥና ከውጭ ገንዘባቸውን እና ንብረታቸውን ኢትዮጵያን ለማዳከም የሚያዋጡ ኃይሎች አንድ ሀገር ብቻ እንዳላቸው አውቀው ከድርጊታቸው ሊቆጠቡ ይገባል ሲሉ ይመክራሉ፡፡

ሌላው አቶ አብዱሰላም መሐመድ ከፋፈን ዞን ጉርሱም ወረዳ የመንግሥት ሠራተኞችን ውክልና የያዙ የምክክሩ ተሳታፊ ናቸው።

ከምክክሩ ኢትዮጵያም ሆነች የሶማሌ ክልል ሕዝብ ተጠቃሚ ነው የሚሉት አቶ አብዱሰላም፤ ከዚህ በፊት ባልነበረ መልኩ የሶማሌ ክልል ሕዝብ እንዲህ ተሰብስቦ የኢትዮጵያን ችግር አንድ ላይ ሆነን እንፍታ በማለት ምክክር መጀመሩ እጅግ አስደስቶኛል ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

የምክክር ሂደቱ በራሱ የኢትዮጵያ ችግር የሶማሌ ክልል ሕዝብ ችግር፤ የሶማሌ ሕዝብ ችግርም የኢትዮጵያ ችግር መሆኑን አመላካች ነው በማለት፤ ለመፍትሄውም በጋራ በመቆም ጠንካራ ሀገር ለመገንባት ያስችላል ብለዋል።

ከዚህ በፊት በሌሎች ክልሎች ስለተካሄደው ምክክር መስማታቸውን በማንሳት ትንሽ ትልቅ ሳይል ሁሉን አሳታፊ ምክክር መካሄዱ ለምክክሩ ስኬት ወሳኝ መሆኑንም ነው የሚገልጹት።ሌሎች ክልሎች ላይ ምክክሩን በማካሄድ አንድነትን ማረጋገጥ ይገባልም ይላሉ፡፡

ውይይቱ ለሀገራዊ አንድነት እና ለጠንካራ ሀገረ መንግሥት ግንባታ ፋይዳ እንዳለው በመግለጽ፤ በምክክር የየግል ሃሳባችን ተደምሮ ወደ ማኅበረሰብ አድጎ እና በክልል ደረጃ ተዋቅሮ መምጣቱ በቀጣይም በሀገር አቀፍ ደረጃ ተጨምቆ የሚቀርብ መሆኑ ኢትዮጵያ ተስፋ ያላት ሀገር መሆንዋን ያመላክታል ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

ውይይት ከፍተኛ ፋይዳ ያለው መሆኑን ከዚህ ምክክር መገንዘብ ይገባል ያሉት አቶ አብዱ ሃሰን፤ ችግር ካለም ጠረጴዛ ላይ ቁጭ ብለን በመመካከር መፍታት ልማዳችን ሊሆን ይገባል ነው ያሉት፡፡

ቀደም ሲል በንግድ ሥርዓቱ ላይ ጥያቄዎች ነበሩን የሚሉት ደግሞ ከኪቲባ ቀብሪበያህ የመጡት የነጋዴዎች ተወካይ አቶ አሕመድ መሐመድ ናቸው።

በተፈጠረው ዕድል ያሉንን አጀንዳዎች ማሰባሰብ ችለናል የሚሉት አቶ አሕመድ፤ ምክክሩ የሶማሌ ክልልን እንደ ክልል ተጠቃሚነቱን ለማረጋገጥ እና አንድነትን ለመገንባት የሚረዳ ነው ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ነጋዴ በመሆኔ የወደብ ጉዳይ ያሳስበኛል ብለውም፤ የወደብ ጥያቄም ሊመለስ የሚችለው እኛ ኢትዮጵያውያን በመጀመሪያ አንድነታችንን ማረጋገጥ ስንችል ነው ሲሉ ተናግረዋል፡፡

ከምክክሩ ብዙ እናተርፋለን፤ በጥቂቱ ካተረፍን እንኳን ሰላም፣ አንድነት፣ ወንድማማችነት በድምሩም ሀገራዊ መግባባት ላይ እንደርሳለን ሲሉ ይገልጻሉ፡፡

በተሳተፍንበት ምክክር ላይ እንደተመለከትኩት የምክክሩ ሂደትና አሳታፊነት የሚደነቅ ነው፤ ሆኖም ቀሪ ክልሎች ሊሳተፉ ይገባል ብለዋል።ቀሪ ክልሎች ሲሳተፉ ሀገራችን ሙሉ ሰላም ታገኛለች ብዬ አስባለሁ ሲሉም ተናግረዋል፡፡

# ፍርድ ቤቱ ፈጣን እልባት ለመስጠት የሚያስችል አሠራር መዘርጋቱን ገለጸ

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- የተቀዱ ክርክሮችን ወደ ጽሁፍ ለመቀየር የሚያስችል ሶፍት ዌር በማበልጸግ ወደ ተግባር በማስገባቱ የሥራ ጫና መቀነሱን፣ መዝገቦች በተያዘላቸው ጊዜ እልባት እንዲያገኙ ማገዙን የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ገለጸ።

የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የ2016 በጀት ዓመት አፈጻጸም ግምገማ እና የ2017 ዓ.ም እቅድ ትውውቅ መርሀ ግብር ትናንት ባካሄደበት ወቅት፤ የፍርድ ቤቱ ፕሬዚዳንት ወይዘሮ ሌሊሴ ደሳለኝ፤ የቴክኖሎጂ አጠቃቀምን በማሳደግ የዳኝነትን አገልግሎት ቅልጥፍና ለማሳደግ እና ተደራሽ ለማድረግ ትኩረት መሰጠቱን ተናግረዋል።

ከአርተፊሻል ኢንተለጀንስ ጋር በመተባበር የተቀዱ ክርክሮችን ወደ ጽሁፍ ለመቀየር የሚያስችል ሶፍት ዌር በማበልጸግ ተግባራዊ የተደረገው አሰራር የዳኝነት አገልግሎት ቅልጥፍናን ማሳደግ መቻሉን ጠቁመዋል።

የሥራ ጫናን መቀነስ አስችሏል፣ መዝገቦች በተያዘላቸው ጊዜ ዕልባት እንዲያገኙ በማድረግ ጉልህ አስተዋጽኦ አበርክቷል ብለዋል።አሠራሩ ሳይዘረጋ በመቆየቱ ተገልጋዮች በቃል ያደረጓቸው ክርክሮች ወደ ጽሁፍ እስኪገለበጡ ብዙ ጊዜ ለመጠበቅ ይጉላሉ እንደነበርም ነው የጠቆሙት፡፡

በ2017 ዓ.ም ስድስት ችሎቶች ላይ ስማርት ችሎቶችን ለማደራጀት ታቅዶ እየተሠራ እንደሚገኝ በመጠቆምም፤ ለተግባሩ ምቹ የማድረግ ሥራ መሠራቱንም ወይዘሮ ሌሊሴ ተናግረዋል።

ዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመጠቀም የዳኝነት አገልግሎት ተደራሽነትን ማሳደግ ትኩረት ይደረግበታል ያሉት ፕሬዚዳንቷ፤ በቪዲዮ ኮንፈረንስ የሚሰጥ የዳኝነት አገልግሎት ማጠናከር፣ በቴክኖሎጂ የተደገፈ ድምጽን ወደ ጽሁፍ የመቀየር አገልግሎት ማስፋፋት፤ በቴክኖሎጂ በመታገዝ ዘመናዊ የመረጃ አያያዝን ሥርዓት ማጠናከር ከትግበራዎቹ መካከል እንደሚጠቀሱም ነው የገለጹት።

ዳኞች መደበኛ የሥራ ጊዜ ዝግ በሆነበት ነሐሴና መስከረም ወራቶች በዕረፍት ጊዜያቸው በመጠቀም ለሁለት ሺህ 485 መዛግብት እልባት መስጠት መቻላቸውንም ነው የጠቆሙት።

የዳኞችን ነጻነት እና ገለልተኝነትን የሚሸረሽሩ ተግባራትን ለመከላከል ትኩረት መደረጉንም ወይዘሮ ሌሊሴ አመልክተዋል። የዳኝነት ነጻነት ሊሸረሽሩ የሚችሉ ህጎችን በተመለከተ የዳሰሳ ጥናት ለማከናወን መታቀዱም ተጠቅሷል።

ለፍርድ ቤቱ አገልግሎት የሚመደበው በጀት ፍላጎትን ያሟላ አለመሆኑ፤ በግልጽ ችሎት ለማስቻል በቂ የቢሮና የማስቻያ አዳራሽ አለመኖር፤ ያሉ የችሎት አዳራሾች በእድሜ ብዛት (በእርጅና) ምክንያት ለተገልጋዮችና ለዳኞች ምቹ አለመሆንና በአፋጣኝ እድሳት የሚፈልጉ መሆናቸው ካጋጠሙ ተግዳሮቶች መካከል ተጠቃሽ መሆናቸውን ጠቅሰዋል።

የዳኞችና የመዝገብ ጥምርታ አለመመጣጠንና የዳኞች እጥረት፤ የአስተዳደር ሠራተኞች አለመሟላት፣ በአንዳንድ ዳኞችና ሠራተኞች ተቀራራቢ አመለካከት፣ እውቀት፣ ክህሎትና በቁርጠኝነት የመፈጸም ውስንነት መኖር ፈተና እንደነበርም ነው የተገለጸው።

የ2016 በጀት ዓመት 30 ሺ መዛግብትን ለመፈጸም ታቅዶ እንደነበር አስታውሰዋል። ሆኖም የዳኞች ቁጥር በቂ ባለመሆኑ ምክንያት እቅዱን በመከለስ 20 ሺ 784 መዝገቦች እንዲሠሩ ታቅዶ 24 ሺ 853 መዛግብት ላይ እልባት ተሰጥቷል ብለዋል። ወደ ተያዘው በጀት ዓመት የተሻገሩ ሰባት ሺህ 136 መዛግብት መኖራቸውንም አመልክተዋል።

# በጌዴኦ ዞን የሚገኙ የቱሪዝም መዳረሻ ስፍራዎችን በማልማት ተጠቃሚ ለመሆን እየተሠራ ነው

**ሳሙኤል ወንደሰን**

ዲላ፡- በዞኑ የሚገኙ የቱሪዝም መዳረሻ ስፍራዎችን በማልማት ዘርፉን ውጤታማ ለማድረግ እየተሠራ እንደሆነ የጌዴኦ ዞን ባህልና ቱሪዝም መምሪያ አስታወቀ።

በመምሪያው የባህል፣ ታሪክ፣ ቅርስ ጥናትና ልማት ቡድን መሪ አቶ ብርሃኑ ይርባ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ የጌዴኦ የቱሪስት መስህቦች በርካታ ናቸው።ከትክል ድንጋይ መካነ ቅርሶች መካከል ቱቲፈላ፣ ጨልባ ቱቲቲ፣ የሴዴ ትክል ድንጋይ መካነ ቅርሶች ይገኙበታል፡፡

በተለይ ቀልብን ከሚስቡ የቱሪዝም ሀብቶች መካከል የጌዴኦ ባህላዊ መልክዓ ምድር በእጅጉ አስደማሚ መሆኑን ገልጸው፤ እነዚህን የቱሪዝም መዳረሻ ስፍራዎችን በማልማት ዘርፉን ውጤታማ ለማድረግ እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል።

የዋሻ ላይ ስዕሎች፣ ፏፏቴዎች ፣ ፍልውሃ፣ የጌዴኦ የዘመን መለወጫ ደራሮ በዓል የቱሪስት መዳረሻ ሥፍራዎችና በዓላት መሆናቸውን ገልጸው፤ በአካባቢዎቹ የመንገድ፣ የውሃ፣ የመብራትና ምቹ የማረፊያ ሥፍራዎች እንዲኖሩ ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብር እየተሠራ ነው ብለዋል።

በእነዚህ ስፍራዎች ወጣቶች ተደራጅተው የሥራ እድል ተጠቃሚ እንዲሆኑ የመስሪያ ቦታ እየተዘጋጀ መሆኑን የገለጹት አቶ ብርሃኑ፤ በባህላዊ አልባሳት፣ በቱር ጋይድ፣ በእጅ ሥራ ሙያ እና በሌሎች ተያያዥ ዘርፎች ተሰማርተው ከራሳቸው አልፈው ቤተሰባቸውን እንዲደግፉ ከክልል ቢሮ ጋር በትብብር እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል።



**አቶ ብርሃኑ ይርባ**

የጌዴኦ መልክዓ ምድር ቅርስ የማኅበረሰቡን መስተጋብር፣ አኗኗር ከማሳየቱም ባለፈ የበርካታ አእዋፋት፣ እንስሳትና አዝርዕት መገኛ ሲሆን፤ ሰው ከተፈጥሮ ጋር እንዴት መኖር እንደሚችል የሚያሳይ ነው ብለዋል።

ቅርሱን በዓለም ቅርስነት ለማስመዝገብ ከ2005ዓ.ም. ጀምሮ እንቅስቃሴ ሲደረግ መቆየቱን ገልጸው፤ በሪያድ በተካሄደው 45ኛው የዩኔስኮ የዓለም ቅርስ ኮሚቴ የዓለም ቅርስ ሆኖ እንደተመዘገበ አቶ ብርሃኑ ይርባ ገልጸዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የገቢ እቅዱን ለማሳካት የታክስ መሠረቱን ማስፋት፤ ሕገወጥነትንም መከላከል የግድ ያስፈልጋል!

በ2017 በጀት ዓመት መንግሥት የሀገር ውስጥ ገቢን አንድ ነጥብ አምስት ትሪሊዮን ለማድረስ ታቅዷል። ይህንን እውን ለማድረግ ደግሞ ወደ ታክስ ሥርዓቱ ያልገቡትን በማስገባት፣ አዳዲስ የታክስ አይነቶችን ተግባራዊ በማድረግ፣ የታክስ አስተዳደር ሥርዓትን በማዘመንና ታክስ በመሰብሰብ፣ የሚወጣ ወጪን ውጤታማ በማድረግ፣ የታክስ ሥርዓቱንም ወደ ክልሎች በማውረድ ያቀደውን ገቢ ለማሳካት አቅጣጫ ተቀይሶ እየተሠራ ነው።

ምክንያቱም መንግሥት የዜጎችን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ እና ፖለቲካዊ እድገትን የማፋጠን ከፍተኛ ሃላፊነት አለበት። ይሄን ኃላፊነት ለመወጣት ደግሞ የራሱ የገቢ ምንጭ ያስፈልገዋል። በዚህ መልኩ በአንድ ሀገር ለመንግሥታዊ ሥራዎች ማስኬጃ ሀብት የማሰባሰቢያ የገቢ ምንጮች መካከል ዋነኛው ግብር ነው።

ለዚህም ነው በአግባቡ ግብር መሰብሰብ የቻለ ሀገር የተፋጠነ ልማት ማከናወን የሚችለው፤ የተረጋጋች ሀገርንም ሲፈጥር እና አስተማማኝ ሰላምና ጸጥታንም ሲያረጋግጥ የሚታየው። ይሄ በማድረጉም ልማትን ያስቀጥላል፤ የተረጋጋና ቀጣይነት ያለውን ብልጽግናንም ያመጣል።

ግብር የዜጎች ሁሉ መብትም ግዴታም ነው። በአንድ ሀገር የተረጋጋ መንግሥታዊ ሥርዓት እንዲኖር፣ ዜጎች ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ተግባሮቻቸውን ሰላማዊ በሆነ መንገድ ማከናወን እንዲችሉና በግለሰብ ደረጃ ሊሟሉ የማይችሉና የጋራ መገልገያ የሆኑ እንደ መንገድ፤ ጸጥታና ደህንነት፤ ትምህርትና ጤና የመሳሰሉ አገልግሎቶችን ማስፋፋት የሚቻለው አስተማማኝ ግብር ሲኖር ነው።

በአጠቃላይ ግብር ዘርፈ ብዙ ጠቀሜታዎች ያሉት እና የመንግሥታት ሀገር የመምራት አቅም እና ብቃት የሚመዘንበት ብቻ ሳይሆን፤ የአንድ ሀገር የኢኮኖሚ ግስጋሴ የሚለካበትም ቁልፍ ተግባር ነው። በመሆኑም፣ ያለ ግብር መንግሥት ሊንቀሳቀስ፣ ሀገርም ልትለማ አትችልም።

ስለዚህ ግብር መክፈል ለሀገር ዕድገትና ለዜጎች ሁለንተናዊ መብቶች መረጋገጥ ካለው ፋይዳ አንጻር አስፈላጊ ከመሆኑም ባሻገር በአንዲት ሉዓላዊ ሀገር ውስጥ ግብር መክፈል ግዴታም ጭምር ነው። ይህንም ተግባራዊ አለማድረግ ደግሞ የወንጀልና አስተዳደራዊ ቅጣቶችንም ያስከትላል።

በኢፌዴሪ ሕገ መንግሥት ስለ ግብር አስፈላጊነትና ግዴታ ከተደነገገው በተጨማሪ በፌዴራል ታክስ አስተዳደርር አዋጅ ቁጥር 983/2008 አንቀጽ 116 እና በተመሳሳይ ድንጋጌዎች ግብርን አለመክፈል፤ ማጭበርበር፣ ግብር መሰወር፣ ቫት ማጭበርበር እና በጠቅላላው ከታክስ ጋር ተያይዘው የሚፈጸሙ ወንጀሎች በእስር እና እንደየ ወንጀሉ ክብደት በብርም የሚያስቀጡ ናቸው። ግብር ማጭበርበርና መሰወር ሕጋዊ ተጠያቂነትን የሚያስከትል ቢሆንም በሀገራችን ከግብር ጋር ተያይዞ በርካታ ወንጀሎች ይፈጸማሉ። ይህ ደግሞ መንግሥት እሰበስበዋለሁ ብሎ ያቀደውን የግብር መጠን እንዳይሰበስብ እንቅፋት ይሆናል።

ለአብነትም የሽያጭ መጠንን ዝቅ በማድረግ የሚፈጸም ግብር መሰወር፤ ግዢን ዝቅ በማድረግ የሽያጭ መጠን እንዲቀንስ እየተደረገ የሚፈጸም የግብር ስወራ፤ የተጨማሪ እሴት ታክስ የተለያዩ የማስከፈያ ምጣኔዎች ያለአግባብ በማቀያየር የሚፈጽም የግብር ስወራ፤ የተሰበሰበን ታክስ (VAT) ለመንግሥት አለመክፈል፤ ከውጭ ወደ ሀገር ውስጥ የሚገቡ ዕቃዎች በሕገወጥ መንገድ በማስገባት ሊሰበሰብ የሚገባ የተጨማሪ እሴት ታክስ ማስቀረት፤ ሐሰተኛ የታክስ ተመላሽ መጠየቅ፤ በሀሰተኛ ደረሰኝ ገቢ መሰብሰብ እና የመሳሰሉት የግብር ሥራዎችና ማጭበርበሮች ይከናወናሉ።

እነዚህ ተግባራት በየአመቱ የሚፈጸሙ የግብር ማጨበርበርያ ስልቶች ሲሆኑ በዚህም መንግሥት በርካታ ገቢዎችን እንዲያጣ ምክንያት የሚሆኑ ናቸው። ይህ ደግሞ እንደሀገር የተቀየሱ እቅዶች በአግባቡ ተግባራዊ እንዳይሆኑ በማድረግ አድገትን ወደ ኋላ የሚጎትት ነው።

በልማት ግስጋሴ ውስጥ የምትገኘው ኢትዮጵያ እድገት እና ብልጽግናዋን ለማሳካት በቂ የገንዘብ ምንጭ ያስፈልጋታል። ዋነኛው የገቢ ምንጭ ደግሞ የሀገር ውስጥ ገቢ ነው። ዘንድሮ እንደ ሀገር የተያዘው የገቢ ዕቅድ 1 ነጥብ 5 ትሪሊዮን ብር ነው። ይህ እቅድ ሀገሪቱ በ2016 በጀት ዓመት ካስገባችው ጠቅላላ ገቢ ከሁለት እጥፍ በላይ ነው።

ስለዚህም የታየዘው እቅድ ግዙፍ ከመሆኑ አንጻር ከወትሮው በተለየ መልኩ ጠንካራ እንቅስቃሴዎችን ማድረግ ያስፈልጋል። ይህንን እውን ለማድረግ ደግሞ ዜጎች እንዲሠሩ በመበረታት የታክስ መሠረቱን ማስፋት እና በታክስ ማጭበርበር ላይ የሚታዩ ሕገወጥ አካሄዶችን እየተከታተሉ ማረም የግድ ይላል።


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**
ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22
ኢሜል ፡- epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**
አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**
ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ
ወረዳ 06
የቤት ቁጥር 319
ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et
ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**
ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com
ስልክ - 011-126-43-41
ፋክስ - 011-811-13-15
የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**
ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ
ስልክ፡- 011 126 4200
Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**
ወርቁ ማሩ
Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**
ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73
ፋክስ - 011-126-58-12
ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**
ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፡- ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ለመሠረተ ልማት ባይተዋር የሆኑ የጋራ መኖሪያ ቤቶች ጉዳይ

ሚሉዲ ከኳስ ሜዳ

መንግሥት የከተሞችን የመኖሪያ ቤት እጥረት ለመፍታት የተለያዩ የልማት ፕሮጀክቶችን ቀርፆ እየሠራ ይገኛል። በተለይም የሀገሪቱም ሆነ የአፍሪካ መዲና ብሎም የተለያዩ ዓለም አቀፍ ተቋማት መቀመጫ በሆነችው አዲስ አበባ የሚስተዋለውን የመኖሪያ ቤት ችግር ለመፍታት ያስችል ዘንዳ የጋራ መኖሪያ ቤቶችን በስፋት በመገንባት ለተጠቃሚዎች ማቅረቡ ለብዙዎች እፎይታን ሰጥቷል።

ሆኖም እድል ቀንቷቸው የመኖሪያ ቤት ባለቤት ለመሆን የበቁ በርካታ የከተማዋ ነዋሪዎች እንዳሉ ሁሉ አሁንም የመኖሪያ ቤት በተስፋና በጉጉት እየጠበቀ ያለው ነዋሪ ቁጥር በቀላሉ የሚገለፅ አይደለም። በርካቶች ነዋሪዎች የመኖሪያ ቤት ባላገኙበት ሁኔታ የመኖሪያ ቤት ፈላጊው ቁጥር እየጨመረ ይገኛል።

ለጽሁፌ መግቢያ ያህል ይህን አነሳሁ እንጂ የዛሬው ዋነኛ አጀንዳዬ ግንባታቸው ተጠናቆ ለተጠቃሚዎች በተላለፉት የጋራ መኖሪያ ቤቶች መንደሮች ያለው ስር የሰደደ የመሠረተ ልማት ችግር ጉዳይ ነው። እርግጥ ነው በተለይም በመሃል አዲስ አበባ የተገነቡት አብዛኞቹ በሚባል ደረጃ ውሃ፤ መብራት፤ መንገድና መሰል ለኑሮ ወሳኝና አንገብጋቢ የሆኑ መሠረተ ልማቶች ተሟልቶላቸው ለነዋሪዎች የተላለፉ ናቸው።

አንዳንዶቹም ነዋሪዎቹ ከገቡ በኋላ በሂደት እየተሟላላቸው የሕዝቡም ጥያቄዎች ምላሽ ያገኙባቸው እንዳሉ እረዳለሁ። ለዚህ ፅሁፍ መነሻ የሆነኝ ግን በተለይ በከተማዋ ዳርቻዎች የተገነቡና በቅርቡ ወደ ኦሮሚያ ክልል በተከለሉ የጋራ መኖሪያ ቤቶች መንደሮች የማስተውለው የመሠረተ ልማት ችግር ነዋሪውን ለከፍተኛ እንግልት እያደረገ ያለበት ሁኔታ ነው።

ለዚህ አብነት አድርጌ የማነሳውም ከስድስት ዓመት በፊት ለተጠቃሚዎች በእጣ የተላለፉትን የኮዬ ፈጬ ሁለት የጋራ መኖሪያ ቤቶችን መንደር ነው። እንደሚታወቀው በወቅቱ በተፈጠረው የፖለቲካ ችግር ምክንያት እጣው ቢወጣም ከሁለት አስርት ዓመታት በላይ በትዕግስት ጠብቆና ከሌለው ጉርሱ ቀንሶ ቆጥቦ ቤት የተሰጠው ባለእድለኛ ቤቱን እጁ ማስገባት የቻለው ከረጅም ጊዜ ቆይታ በኋላ ነው።

ከ50 ሺ በላይ ቤቶችን ባካተተው በዚህ ግዙፍ ፕሮጀክት ታዲያ ነዋሪዎች ቁልፋቸውን ተረክበው ወደ ቤታቸው ሲገቡ ከነበረባቸው የቤት ኪራይ ጫና ተላቀን እንደማንኛውም ዜጋ በጊዜ ሂደት አስፈላጊ መሠረተ ልማት ተሟልተው የተመቻቸ ኑሮ እንኖራለን በሚል ተስፋ ነበር።

ሆኖም ጊዜ ጊዜን እየወለደ ቢሄድም በዚህ መንደር ውሃ፣ መብራት፣ መንገድ፣ ጤና ጣቢያና ትምህርት ቤት እንዲሁም የትራንስፖርት አገልግሎት ሳያገኙ በመቅረታቸው ነዋሪው በብዙ የኑሮ ቀውስ ውስጥ እንዲኖር ተገዷል። እርግጥ ነው ከ50 ለሚልቁት ነዋሪዎች ቁጥር ባይመጥንም አንድ መለስተኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ተገንብቶ በቅርቡ ሥራ ጀምሯል፤ መብራትም ለአንድ ህንፃ ማለትም ከ40 እስከ 60 ለሚደርሱ ቤቶች አንድ ቆጣሪ ተሰጥቶ የሃይል ጥያቄ በጥቂቱ ተመልሷል።

ይሁንና ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ነዋሪው ሙሉ ለሙሉ ወደ መኖሪያ ቤቱ እየገባ መሆኑን ተከትሎ የተሰጠው የሃይል መጠን ከተጠቃሚው ብዛት ጋር የማይመጣጠን ከመሆኑ ጋር ተያይዞ አብዛኛውን ጊዜ በጨለማ ለማደርና እንደ ከሰል ባሉ የሃይል አማራጮች ለመጠቀም ተገዷል።

ከሁሉም በላይ ግን አንገብጋቢ የሆነውና ነዋሪውን ያማረረው የንፁህ መጠጥ ውሃ አገልግሎት ጉዳይ ነው። በአካባቢው ሰፊ የሆነ የከርሰ ምድር ውሃ ሀብት እንዳለ የሚነገር ቢሆንም፤ በተጨባጭም በአቅራቢያ ባሉ አካባቢዎች ላይ ውሃው ወጥቶ ጥቅም ላይ እንደዋለ ቢታወቅም በእነዚህ መኖሪያ ቤቶች ውስጥ የሚኖሩ ነዋሪዎች ግን ውሃ የማግኘት ተስፋቸው የውሃ ሽታ ሆኖ ቀርቶባቸዋል።

ከካሳ ጥያቄና ከሌሎችም ምክንያቶች ጋር ተያይዞ ከሁሉም መሠረተ ልማቶች በባሰ ሁኔታ የውሃ መስመር ዝርጋታው እንዲዘገይ ተደርጎ ነበር፤ እሺ ይህስ ይሁን። ዝርጋታው ከተጠናቀቀ በኋላ ደግሞ በአሁኑ ወቅት ቤቶቹን ተረክቦ እያስተዳደረ ያለው የመንግሥት አካል መስመሩ እንዲገናኝ አስደርጎ ውሃውን ማስለቀቅ ሲገባው ይህን አለማድረጉ ሕዝቡ በየእለቱ ከፍተኛ ወጪ እንዲያወጣ አስገድዶታል። አንድ ጄሪካን ውሃ (ሊያውም ለመጠጥ አገልግሎት የማይውል) ከ15 እስከ 30 ብር በመግዛት የውሃ ቸርቻሪዎች ሲሳይ ሆኗል።

በሌላ በኩል የኮሪደር ልማቱንና መልሶ ልማቱን ተከትሎ በአካባቢው የነዋሪዎች ቁጥር በከፍተኛ ደረጃ እየጨመረ ይገኛል። ይህንን የሕዝብ ብዛት በሚመጥን ደረጃ የመንገድ መሠረተ ልማት የተገነባበት ሁኔታም የለም። በዚህ የተነሳ ከቱሊዲምቱና ቀድሞ ከተገነባውና ከለማው ኮዬ አንድ ሞልተው ከሚነሱ አውቶብሶችና ታክሲዎች ውጪ መነሻቸው ኮዬ ሁለት የሆነ ምንም አይነት ትራንስፖርት አገልግሎቶች አለመኖራቸውም ሌላው የነዋሪዎቹን ችግር ከድጡ ወደ ማጡ ያደረገባቸው ብል ማገናን አይሆንብኝም። አልፎ አልፎ ውር ውር የሚሉት ታክሲዎችም ቢሆኑ ተቆጣጣሪ የሌላቸው ከመሆኑ ጋር ተያይዞ እንዳሻቸው ታሪፍ የሚጨምሩበት ሁኔታ የሕዝቡን የኢኮኖሚ አቅም እየተፈታተነው ይገኛል።

የሚገርመው ነገር ደግሞ ይህ ፕሮጀክት ግዙፍና ወደፊት የድሬዳዋ ያህል በርካታ የሕዝብ ቁጥር ይሸከማል ተብሎ የተሠራ የመሆኑን ያህል ምንም አይነት መሠረተ ልማት ያለመዘርጋቱ ነው። እንደሚታወቀው ደግሞ እነዚህ ቤቶች የተገነቡት ከከተማ እጅግ ርቀው በመሆናቸው የህክምና አገልግሎት ለማግኘት (በሽታው የቱንም ያህል አጣዳፊ ቢሆን) ረጅም ርቀት መጓዝ የግድ ሆኗል።

እርግጥ ነው ኮዬ አንድ አነስተኛ የመንግሥት ጤና ጣቢያ አለ፤ እሱም ቢሆን ለግዙፉ የኮዬ ሁለት ሕዝብ ቀርቶ ቀድመው ኑሮ ላጣጣሙት የኮዬ አንድ ነዋሪዎች እንኳን በተደራሽነትም፤ በባለሙያና በአቅምም የማይመጥን ሆኖ አግኝቼዋለሁ።

ይህ ግብር ከፋይ የጋራ መኖሪያ ቤት ነዋሪ እንደማንኛውም ዜጋ እነዚህን የመሠረተ ልማትና የመልካም አስተዳደር ጥያቄዎች ምላሽ እንዲያገኙለት በተደጋጋሚ ለሚመለከታቸው የመንግሥት አካላት አቅርቧል። ይሁንና በየጊዜው የተለያዩ ምክንያቶችን ከመደርደርና ያልተጨበጠ ተስፋ ከመስጠት ባለፈ ወደ ተግባር የተለወጠ ልማት ማየት አልቻለም።

በአንፃሩ ደግሞ ለልማትም ሆነ ለሌሎች መንግሥታዊ ሥራዎች ሕዝቡ በተጠየቀ ቁጥር የቱንም ያህል የኑሮ ጫና ውስጥ ቢሆን የበኩሉን ድጋፍ እያደረገ ይገኛል። በመሆኑም መንግሥት በመሃል ከተሞች ላይ እያከናወነ እንዳለው ሰፊና አበረታች የልማት ሥራ ሁሉ ለመሠረተ ልማት ባይተዋር በሆኑና ከተማ ዳርቻ ለሚገኙ የጋራ መኖሪያ ቤት ነዋሪዎች መሠረታዊ ጥያቄዎች ምላሽ ሊገባ ይገባል የሚል እምነት አለኝ!። በተለይ ደግሞ የውሃ ጉዳይ ጊዜ የማይሰጥና አንገብጋቢ ከመሆኑ አንፃር ቅድሚያ ሊሰጠው ይገባል ባይ ነኝ!፡

ዜና

# አደጋ የደቀነው...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ስርጭት ምን ደረጃ ላይ ይገኛል፣ ችግሩን ለመከላከል ምን እየተሰራ ነው? የሚያስከትለው የወንጀል ተጠያቂነትስ ምንድነው? በሚሉት ጉዳዮች ዙሪያ የዘርፉ ምሁራን ሃሳባቸውን አጋርተውናል።

በጅማ ዩኒቨርሲቲ በሚዲያና ኮሙኒኬሽን ትምህርት ክፍል መምህር ፋሚ ጀማል እንደሚገልጹት፤ የጥላቻ ንግግር በዘር፣ በሃይማኖት፣ በጎሳ፣ በፆታ ወይም በፖለቲካዊ እሳቤ ላይ ያነጣጠረ ነው። በሁለት ግለሰቦች ከሚደረግ የቃላት ልውውጥ እስከ ትልልቅ መገናኛ ብዙኃን እስከመሰራጨት ሊደርስ ይችላል። ይህም የሀገርን እድገት የሚያናጉ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ መዘዞች አሉት።

የጥላቻ ንግግርና ሀሰተኛ መረጃ በዜጎች መካከል አለመግባባትን፣ አለመተማመንንና መለያየትን ይዘራል። ይህንን ተከትሎም ግለሰቦች ወይም ማህበረሰቦች መድልዎና መገለል ሊደርስባቸው ይችላል የሚሉት መምህር ፋሚ፤ የጥላቻ ንግግር የፖለቲካ ክፍፍልን በማጎልበት የተረጋጋ ጥምረት ወይም ሁሉን አቀፍ አስተዳደር ለመፍጠር የሚደረገውን ጥረት አስቸጋሪ እንደሚያደርገው ይገልጻሉ።

እንደ መምህር ፋሚ ገለጻ፤ የጥላቻ ንግግርና ሀሰተኛ መረጃ ሀገራዊ አንድነትን በማናጋት ዜጎች በመንግሥት ተቋማት ላይ የሚኖራቸውን አመኔታ የሚያሳጣ ነው። የቆዩ ቅሬታዎችን በማቀጣጠል በብሔረሰቦች መካከል ግጭት እንዲፈጠር በማድረግ ወደ ብጥብጥ እንዲሸጋገር ያደርጋል። በዋናነት መረጃው የሚሰራጨው በማህበራዊ ሚዲያ አማካኝነት መሆኑ ታይቶ በማይታወቅ ፍጥነት ግጭት እንዲፈጠር ሊያደርግ የሚችልበት ዕድል ከፍተኛ ነው።

በኢትዮጵያ ከፋፋይ ንግግሮች በተለይም በማህበራዊ ሚዲያ ላይ በስፋት ይታያሉ፤ በዚህም የተለያየ ብሔር፣ ቋንቋ፣ እምነትና የባህል ልዩነቶች በመኖራቸው የጥላቻ ንግግር የሚያስከትለው አደጋ የጎላ ነው። የዲጂታል ይዘቶች ስርጭትና ፍጆታ ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ በመምጣቱ በተለያዩ የኦንላይን ሚዲያ መድረኮች የተሳሳቱ መረጃዎች መስፋፋት በኢትዮጵያ ባለፉት ጥቂት ዓመታት ውስጥ የብሔር ግጭቶችን በማባባስ በተለያዩ ቡድኖችና ሕዝቦች መካከል አለመተማመን እንዲፈጠር አድርጓል ነው የሚሉት መምህር ፋሚ።

እንዲሁም መቻቻልንና በዜጎች መካከል ያለውን አብሮ የመኖር እሴት በመሸርሸር ሀገሪቱ አሁን ላለችበት አለመረጋጋትና ብጥብጥ አሉታዊ አስተዋፅኦ ሲያደርግ ይስተዋላል የሚሉት መምህሩ፤ በተለይም ወጣቶች የተሳሳተ መረጃ ወጥመድ ውስጥ በስፋት እየወደቁ መሆናቸው በሀገሪቱ የሚገኙ የዜና አውታሮች በተደራጀ መልኩ መረጃን የማጣራት ሥርዓት ባለመዘርጋታቸው ችግሩ እየተባባሰ እንደመጣ ማሳያ እንደሆነ ይናገራሉ።

መምህር ፋሚ ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሀሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመቅረፍ ነባር ሚዲያዎች ትልቅ ጥረቶችን እያደረጉ መምጣታቸውን በማንሳት እነኝህን ተነሳሽነቶች በማጠናከር በቴክኖሎጂ የታገዘ ሥራዎች ሊሠሩ ይገባል ይላሉ።

በኢትዮጵያ መገናኛ ብዙኃን ባለስልጣን የዋና ዳይሬክተር ጽህፈት ቤት ኃላፊ የሺወርቅ ግርማ እንደሚናገሩት፤ የጥላቻ ንግግርና የሐሰተኛ መረጃን በማሰራጨት ረገድ የሚታዩ ችግሮችን ለመቅረፍ ባለስልጣኑ በአዋጅ በተሰጠው ኃላፊነት መሰረት በተለያዩ አማራጮች ህብረተሰቡ ምን አይነት መረጃዎችን ማሰራጨትና መጠቀም እንዳለበት የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥራዎችን እየሠራ ነው። ከተለያዩ አካላት በሚመጡ ቅሬታና ጥቆማዎች ላይ ተመርኩዞ በመከታተል ተጠያቂነትን ለማስፈን የሚያከናውናቸው ተግባራትም አሉ።

ባለስልጣኑ በበይነ መረብ የሚሰራጩ የጥላቻና ሀሰተኛ መረጃዎች ያላቸውን የጉዳት ደረጃ በመከታተል ሪፖርት እንደሚያወጣ የሚገልጹት ወይዘሮ የሺወርቅ፤ በዚህም በፖለቲካ፣ በብሔር፣ በማንነት፣ በአመለካከትና በሌሎችም ላይ በማተኮር የተለያዩ የስድብ፣ የዛቻ፣ ክብረ ነክና ሌሎችም ይዘት ያላቸው መረጃዎች እየተሰራጩ እንደሆነ መገንዘብ መቻሉን ያነሳሉ።

እንደ ጽህፈት ቤት ኃላፊዋ ገለጻ፤ እንደ ኤክስ፣ ዩቲዩብና ፌስቡክ ካሉ እና ሌሎችም ተቋማት ጋር በመነጋገር ግለሰቦች ጥቆማ እንዲሰጡ በማድረግ የበይነ መረብ ጥላቻ ንግግርና የሐሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከል የዜጎች የሚዲያ እውቀት (Media Literacy) ከፍ እንዲል ጥረት እየተደረገ ነው።

ከበይነ መረብ ሚዲያዎች መስፋፋትና የተጠቃሚዎች ቁጥር መጨመር ጋር ተያይዞ ባለስልጣኑ በተለያየ ሙያ ውስጥ ለሚገኙ ዜጎች ኃላፊነት በተሞላበት ሁኔታ ሚዲያን ለመጠቀም የሚያስችል ነጻ የግንዛቤ ማስጨበጫ እየሰጠ መሆኑን የሚያነሱት የጽህፈት ቤት ኃላፊዋ፤ በዚህም በአዲስ አበባ፣ በሀዋሳ፣ በድሬዳዋና በሌሎችም የክልል ከተሞች ለዜጎች ግንዛቤ ማስጨበጥ ተችሏል ይላሉ።

በአዲስ አበባ ለሚገኙ የአንደኛና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት የሚኒ ሚዲያ አባላትና መምህራን፣ በተጨማሪም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላትና ለፍትህ አካላትም ስለጉዳዩ ግንዛቤ እንዲጨብጡ ተደርጓል። በቀጣይም ከሬዲዮ አድማጮችና በጋዜጠኝነት ላይ ከሚሰሩ የሙያ ማህበራት ጋር በመተባበር ዜጎች እንዲጠቁሙና ቅሬታ እንዲያቀርቡ እንደሚሠራ ወይዘሮ የሺወርቅ ያመላክታሉ።

ድርጊቶች ተፈጽመው ሲገኙም ከተቋማትና ግለሰቦች የሚመጡ ቅሬታዎችና ጥቆማዎችን በማጣራት ሙያዊ አስተያየት በማከል ለሚመለከተው አካል ተደራሽ ይደረጋል። በዚህም በ11 ክልሎች ቢሮዎችን ከፍቶ ባለሙያዎችን በመመደብ ዜጎች በራሳቸው ቋንቋ ጥቆማና ቅሬታ እንዲያቀርቡ በጥላቻ ንግግርና የሐሰተኛ መረጃ ዙሪያ ግንዛቤ እንዲኖራቸው የሚያደርግ አደረጃጀት ተዘርግቷል ሲሉም ያክላሉ።

የጥላቻ ንግግርና የሐሰተኛ መረጃ ስርጭትን ለመከላከልና ለመቆጣጠር በወጣው አዋጅ ቁጥር 1185/2012 አንቀጽ 4 ማንኛውም ሰው የጥላቻ ንግግርን በብሮድካስት፣ በህትመት ወይም በማህበራዊ ሚዲያዎች ወይም በሌላ ተመሳሳይ ዘዴዎች አማካኝነት በጽሑፍ፣ በምስል፣ በድምጽ፣ ወይም በቪዲዮ እንዳያሰራጭ ይከለክላል።

በአዋጁ አንቀጽ 5 መሰረት፣ ማንኛውም ሰው የሐሰት መረጃን በአደባባይ ስብሰባዎች በብሮድካስት፣ በህትመት ወይም በማህበራዊ ሚዲያዎች ወይም በሌላ ተመሳሳይ ዘዴዎች አማካኝነት በጽሑፍ፣ በምስል፣ በድምጽ፣ ወይም በቪዲዮ ማሰራጨት የተከለከለ ተግባር ነው።

የጥላቻ ንግግርና የሐሰተኛ መረጃ ስርጭት የሚያስከትለውን የወንጀል ተጠያቂነት በተመለከተ በአዋጁ አንቀጽ 7 መሰረት ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 4 መሰረት የተከለከለውን የጥላቻ ንግግር ያደረገ እንደሆነ፣ እስከ ሁለት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት ወይም ከብር 100 ሺህ ባልበለጠ መቀጮ ይቀጣል።

እንዲሁም በጥላቻ ንግግሩ ምክንያት በግለሰብ ወይም በቡድን ላይ ጥቃት የተፈጸመ እንደሆነ፣ ቅጣቱ ከአንድ ዓመት እስከ አምስት ዓመት የሚደርስ ቀላል እስራት ይሆናል። ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 መሰረት ክልከላ የተደረገበትን ተግባር የፈጸመ እንደሆነ፣ እስከ አንድ ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት ወይም ከብር 50 ሺህ ባልበለጠ መቀጮ ይቀጣል።

በአዋጁ መሰረት የጥላቻ ንግግር ወይም የሐሰተኛ መረጃ ስርጭት ወንጀሉ የተፈጸመው ከ5 ሺህ በላይ ተከታይ ባለው የማህበራዊ ሚዲያ ገጽ፣ በብሮድካስት አገልገሎት ወይም በየጊዜው በሚወጣ የህትመት ውጤት ከሆነ፤ ቅጣቱ እስከ ሶስት ዓመት የሚደርስ ቀላል እስራትና ከብር 100 ሺህ ያልበለጠ መቀጮ ይሆናል።

በተጨማሪም ሐሰተኛ መረጃ በመሰራጨቱ ምክንያት በግለሰብ ወይም በቡድን ላይ ጥቃት የተፈጸመ ከሆነ፣ ሁከት ወይም ግጭት የተከሰተ እንደሆነ ከሁለት እስከ አምስት ዓመት በሚደርስ ቀላል እስራት የሚያስቀጣ ይሆናል።

በጥላቻ ንግግር ወይም በሐሰተኛ መረጃ ወንጀል መፈጸም ምክንያት በግለሰብ ወይም በቡድን ላይ ጥቃት ያልተፈጸመ ወይም ያልተሞከረ ከሆነ፣ ሁከት ወይም ግጭት ያልተከሰተ እንደሆነ፣ እና ጥፋተኛውን ለማረም የተሻለ ነው ብሎ ሲያምን ፍርድ ቤቱ በእስራት ምትክ የግዴታ የማህበረሰብ አገልግሎት ሥራን በአማራጭ ቅጣትነት ሊወስን እንደሚችል በአዋጁ ላይ ተደንግጓል።

# ታም ከመማቀቅ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ነው። በየጊዜው የጤንነትን ሁኔታ የማወቅ ልምድ ባለመኖሩ በተለይም ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ በርካቶችን የአካልና የሕይወት ዋጋ ሲያስከፍል እያስተዋልን ነው።

ከ20 ዓመታት በላይ በመምህርነት ሙያ ያገለገሉት መምህር ኃይለኢየሱስ ይሁነኝ፣ ጤናዬ ያለበትን ሁኔታ ልወቅ ብለው ወደ ሕክምና ተቋም ያመሩበትን ጊዜ አያስታውሱትም። የጤና እክል ሲገጥማቸው ወደ ሕክምና ተቋም ከመሄድ ይልቅ “ይሻለኛል” በማለት ጊዜ መስጠትን አሊያም ወደ መድኃኒት ቤት ማቅናትን እንደሚመርጡ ይናገራሉ።

በተደጋጋሚ ዓይናቸውን ሲሰማቸው ያለ ትዕዛዝ ይሆነኛል ብለው ያሰቡትን መነጽር በራሳቸው ፍላጎት ገዝተው ይጠቀሙ እንደነበርም ያስታውሳሉ። “በእናትና በዓይን አይቀለድም” የሚለውን ብሒል ችላ ያሉት መምህሩ፤ የሕክምና ምርመራ ያለማድረግ ልማዳቸው በመጨረሻም ዋጋ አስከፍሏቸዋል።

ቀድመው ቢያውቁት ኖሮ ሳይከፋ ሊከላከሉት የሚችሉት ግላኮማ (የዓይን ግፊት ህመም) ምልክቱን ባስተዋሉ በአጭር ጊዜ ውስጥ የአንድ ዓይናቸውን ዕይታ አሳጣቸው፤ ሁለተኛው ዓይናቸው ላይ ከረፈደ በወሰዱት ቀዶ ህክምና የህክምና ባለሙያዎች እንደነገሯቸው በጊዜው 50 ከመቶ ያህል ዕይታቸውን ማትረፍ የተቻለ ቢሆንም፣ በጊዜ ሂደት ግን የዚህኛው ዓይናቸው የማየት አቅምም አሁን ላይ በእጅጉ መቀነሱን ይናገራሉ።

ሙያቸውን አክባሪና በተማሪዎቻቸውም ተወዳጅ የነበሩት የሰውነት ማጎልመሻ መምህሩ ኃይለኢየሱስ ይሁነኝ፤ ከጡረታ እድሜም አልፈው ማገልገል የሚችል አቅም የነበራቸው የአራት ልጆች አባት እንደ ቀድሞው ወጥቶ መግባት፤ እንደ በፊቱ ተማሪዎቻቸውን በፍቅር ማስተማር አልተቻላቸውም።

ለሁለት ዓመታት ያህል አልፎ አልፎ በሰው ርዳታ፣ አንዳንዴ ደግሞ ከስጋት ጋር በራሳቸው ወደ ሥራ ሲወጡ ቆይተው ከጡረታ እድሜ አምስት ዓመታት ቀድመው ቤት ለመቀመጥ ተገደዱ። ቤት መዋል ከጀመሩ በኋላ እርጅና በፍጥነት እንደተጫናቸው፤ ህመም እንደማይለያቸው ነው ያስረዱት።

በአቤት ሆስፒታል ሜዲካል ዳይሬክተርና ድንገተኛና ጽኑ ሕክምና ተባባሪ ፕሮፌሰር ወልደሰንበት ዋጋነው (ዶ/ር)፤ በማኅበረሰባችን ዘንድ ጤናን በተመለከተ ያለው ግንዛቤ አናሳ መሆኑን ያነሳሉ። ግንዛቤ የማስጨበጡ ሥራም በስፋት ያልተሄደበት መሆኑን ይናገራሉ።

በየጊዜው የጤና ምርመራ የማድረግ ልምድ እምብዛም ነው ያሉት ዶክተር ወልደሰንበት፤ ሰዎች ህመም ሳይበረታባቸው አስቀድመው ጤናማ በሆኑ ጊዜ ጠቅላላ ምርመራ የማድረግ ልምዱ ቢኖራቸው በሽታ ሳይጸና አስቀድሞ ለማወቅና ለመከላከል እንደሚረዳ ይጠቁማሉ።

የሕክምና ባለሙያው እንዳስረዱት፤ አንድ ሰው ምንም አይነት የጤና ችግር ባይሰማውም በየስድስት ወሩ መሠረታዊ የሆነ የጤና ምርመራ ቢያደርግ ይመከራል። ሰዎች በተፈጥሯችን በየጊዜው የሚቀያየር ሁኔታ ስላለን ይህንን ለውጥ ለማየት፣ በርትቶ ያልወጣ የጤና እክል ካለም ሳይጸና በፊት ለመለየትና በቀላል ህክምና ታክሞ ለመዳን በእጅጉ ይረዳል።

እንደ ግፊት፣ ኩላሊት፣ ጉበት የዓይን ሕመምና ሌሎችም ተላላፊ ያልሆኑ በሽታዎች በአብዛኛው ጫን እያሉ የሚመጡት በሂደት እንደሆነ የተናገሩት ዶክተር ወልደሰንበት፤ በየጊዜው የመመርመር ባህል የሌለን ከመሆናችን የተነሳ በእነዚህ በሽታዎች በፅኑ የታመሙ ሰዎች በየጊዜው እየተበራከቱ መጥተዋል ይላሉ።

ብዙ በሽታዎች በድንገት ዛሬ የሚከሰቱ ሳይሆኑ በሂደት እየበረቱ የሚሄዱ መሆናቸውን ጠቁመው፤ በሽታን በጊዜ መቆጣጠር ሲቻል ቀድመን ምርመራ ባለማድረጋቸው ህመሙ እየከፋ ሄዶ ብዙዎችን ለከፋ ጉዳት እንደሚዳርግ ይገልጻሉ።

እርሳቸው እንዳሉት፣ አሁን አሁን በዊልቸር የሚሄዱ ሰዎች መበራከትና የፊዚዮቴራፒ ህክምና ማዕከላት በየቦታው መከፈት እንዲሁም የጽኑ ህሙማን ክፍሎች በታካሚዎች መጨናነቅ በማኅበረሰባችን ዘንድ አስቀድሞ የጤና ሁኔታን የማወቅ ልምድ አናሳ መሆን ውጤት መሆኑን ያሳያል።

በርካታ በሽተኞች ወደ ጽኑ ህሙማን ክፍል የሚመጡት ህመማቸውን አክሞ ማዳን በማይቻልበት ሁኔታ ላይ ደርሶ እንደሆነ በማንሳት፤ በሽታ ከፍተኛ ደረጃ ላይ ከደረሰ በኋላ የሚሰጥ ህክምና በታካሚው፣ በህክምናውና በቤተሰብ ላይ ከባድ ጫናን እንደሚያሳድር ይገልጻሉ።

በጣም ውስን ሰዎች በተለይ በመዲናዋ አዲስ አበባ ወደ ግል የጤና ተቋማት በማምራት የጤና ሁኔታቸውን እንደሚመረመሩ የጠቆሙት ዶክተሩ፣ ይህ ልምድ በሌላው ማኅበረሰብ ዘንድም መስፋት እንዳለበት ይመክራሉ።

እያንዳንዱ ሰው በዓመት አንዴ የጤና ምርመራ ማድረግ፣ ከጤና ባለሙያዎች ጋር መመካከር የህክምና ምክር አገልግሎት መውሰድ እንደሚገባውና የጤናው ሥርዓትም ለዚህ አገልግሎት ምቹ ሆኖ መቀረጽ እንዳለበት ሃሳባቸውን ሰንዝረዋል።

በተለያዩ የመንግሥት የጤና ተቋማት የለውጥ ሥራዎች እየተሠሩ መሆናቸውን ያነሱት የሕክምና ባለሙያው፤ ሳይታመሙ የጤና ሁኔታቸውን ለመመርመር የሚመጡትን ለማከም የሚያስችሉ ማዕከላት እየተከፈቱ መሆናቸውን አንስተዋል። ይህም ሰውን ገፊ ሳይሆን ሰዎችን ሳቢ በሆነና ቢሮክራሲ በማይበዛበት የህክምና አሠራር ሰዎችን ለማስተናገድ በሚያስችል ሁኔታ ተግባራዊ መደረግ እንዳለበት ተናግረዋል።

እርሳቸው እንዳሉት፣ ከጤና ጣቢያ ጀምሮ የመንግሥት የጤና ተቋማትም ለዚህ ዝግጁ ሆነው ምቹ የሆነ ከባቢን በመፍጠር የማኅበረሰብን ጤና ለመጠበቅና የጽኑ ህመም አደጋን ለመከላከል ተጠናክረው ሊሠሩ ይገባል።

ሰዎች ስለ ጤና እና ጤና አጠባበቅ ያላቸውን ግንዛቤ ለማሳደግ በሚደረገው ጥረት የጤና ሚኒስቴር፣ መገናኛ ብዙኃንና ሌሎችም የሚመለከታቸው አካላት ብዙ የቤት ሥራ እንደሚጠበቅባቸውም ነው ምክረ ሃሳባቸውን ያቀረቡት።

# የማክሮ ኢኮኖሚ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

ሚኒስቴር አስታወቀ። ባህላዊ የማዕድን ቆፋሮን በማዘመን የምርት ብክነትን በመቀነስ ምርታማነትን የማሳደግ ሥራም እየተሠራ እንደሚገኝም ተጠቁሟል።

የማዕድን ሚኒስትር ዴኤታ አቶ ሚሊዮን ማቲዎስ ለኢትዮያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ መንግሥት ተግባራዊ እያደረገው የሚገኘው የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያ የማዕድናት ምርታማነትን በተለይ የወርቅ ምርትን በከፍተኛ ሁኔታ እያሳደገ ነው።

ከማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው በአነስተኛ ደረጃ ይመረት የነበረው የማዕድን ምርት በከፍተኛ መጠን እያሳደገው ነው፤ በተለይም የወርቅ ምርታማነት በከፍተኛ ደረጃ እያደገ ነው ያሉት ሚኒስትር ዴኤታው፤ ማሻሻያውን ምክንያት በማድረግ በተያዘው በጀት ዓመት ስምንት ነጥብ ስድስት ቶን ወርቅ ለማምረት ታቅዶ እየተሠራ መሆኑን አመልክተዋል።

በዚህም ባለፉት ሶስት ወራት ብቻ የእቅዱን 70 በመቶ ማሳካት መቻሉን ጠቁመው፤ማሻሻያው የማዕድናት አምራቾችን ተጠቃሚ እያደረጋቸው በመሆኑ የተሻሉ ማሽነሪዎችንና ቴክኖሎጂዎችን ገዝተው ወደ ምርት ሂደቱ እየገቡ መሆኑን ገልጸዋል።

የተሻሉ ማሽነሪዎችንና ቴክኖሎጂ መጠቀማቸውም የምርትና የጉልበት ብክነትን በመቀነስ የማዕድን ምርትና ምርታማነት በከፍተኛ ሁኔታ እያሳደገ ነው ሲሉ ተናግረዋል።

ሀገሪቱ ሰፊ የማዕድን ሀብት አላት፤ ያላት ማዕድን ሀብት ለማልማት የህግ ማዕቀፎችንና ፖሊሲዎችን የማሻሻል፤ ተቋማዊ ለውጦችን የማድረግ ሥራ ተሠርቷል ያሉት አቶ ሚሊዮን፤ማዕድናትን በባህላዊና በኢንዱስትሪ በማምረት ምርታማነትን የማሳደግ፤ የሀገሪቱን የውጭ ምንዛሪ ማሳደግና አምራቾች ይበልጥ ተጠቃሚ እንዲሆኑ እየተሠራ ነው ሲሉ አብራርተዋል።

ኢትዮጵያ ያላትን ሰፊ የማዕድን ሀብት አልምቶ ከዘርፉ ማግኘት ያለባትን ጥቅም እንድታገኝ ለማድረግ ባለፉት ስድስት ዓመታት ካፒታል የማከማቸት፤ አዳዲስ የልማት አቅጣጫን የመከተል ሥራ እየተሠራ መሆኑንም ተናግረዋል።

ቀደም ሲል መንግሥት ልዩ ትኩረት ከሚሰጣቸው ዘርፎች ውስጥ የማዕድን ዘርፍ አልተካተተም ነበር፤ ባለፉት ስድስት ዓመታት ግን ዘርፉ ትኩረት ተሰጥቶት እየተሠራበት ነው፤ ትኩረት በመሰጠቱም ዘርፉ እየለማና እያደገ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

እንደ አቶ ሚሊዮን ገለጻ፤ የኢትዮጵያ ማዕድን በአብዛኛው የሚመረተው በባህላዊ መንገድ ነው። በባህላዊ መንገድም በዋናነት ወርቅ፣ ጌጣጌጥና ለግንባታ የሚውሉ ማዕድናት ተመርተዋል። የማዕድን ምርትማነትን ለማሳደግ ባህላዊ የማዕድን አመራረትን የማዘመን፣ በቴክኖሎጂ የመደገፍ ሥራ እየተሠራ ነው።

የባህላዊ አምራቾች ካፒታላቸውን በማጠራቀም ቴክኖሎጂን እንዲጠቀሙ፤ ክህሎታቸውን እንዲያሳድጉ፤ ገቢያቸውን እንዲያሻሽሉ በማድረግ ምርትን የማሳደግ ሥራ እየተሠራ ነው፤ በተያዘው በጀት ዓመትም ስምንት ነጥብ ስድስት ቶን ወርቅ ለማምረት ታቅዷል። ከዕቅዱም ሶስት ሺህ 600 ኪሎ ግራም ያህል የሚመረተው በባህላዊ መንገድ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

የባህላዊ የማዕድን ቁፋሮ ወደ አነስተኛና መካከለኛ እንዲሁም ወደ ከፍተኛ ኢንዱስትሪ እንዲያድግ እየተደረገ መሆኑን አመልክተው፤ባህላዊ የማዕድን አመራረት ዘዴ ከፍተኛ የሆነ የምርትና የጉልበት ብክነት አለው፤ የምርትና የጉልበት ብክነትን ለመቀነስ አመራረቱን የማዘመን ሥራ እየተሠራ ነው ሲሉ ጠቁመዋል።

# “በመጀመሪያው ሩብ...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

እንዲመዘገብ ማድረጉም ነው የተገለጸው። ይህም የተቀመጠው እድገት እንደሚመዘገብ አመላካች ነው ብለዋል ሚኒስትሯ።

በተለይ በወጪ ንግድ፣ በመንግሥት ገቢ ፣ በውጭ ቀጥታ ኢንቨስትመንትና በውጭ ምንዛሬ ግኝት የተሻለ አፈጻጸም ተመዝግቧል። ከወጪ ንግድ አንጻር በተለይ በወርቅ ወጪ ንግድ እጅግ ስኬታማ ሥራ መከናወኑን አብራርተዋል።

ለአብነትም በ2016 በጀት ዓመት ዓመቱን ሙሉ ወደ ብሔራዊ ባንክ የገባው የወርቅ መጠን 4 ቶን ብቻ እንደነበር የተናገሩት ሚኒስትሯ፤ በተያዘው በጀት ዓመት የመጀመሪያ ሶስት ወራት ብቻ 7 ቶን ወርቅ ወደ ብሔራዊ ባንክ መግባቱን ተናግረዋል።

የማክሮ ኢኮኖሚ ማሻሻያው በአጭር ጊዜ ውስጥ ምን ያህል ለውጥ ማምጣቱን አመላካች ስለመሆኑ አብራርተዋል።

የገንዘብ ሚኒስትሩ አሕመድ ሽዴ በበኩላቸው፤ የኢኮኖሚ ማሻሻያው ሰፊ ዝግጅት ተደርጎበት በመተግበሩ ስኬታማ ሆኗል። በአጠቃላይ ያለፉት ሶስት ወራት አፈጻጸም ካለፈው በጀት ዓመት የተሻለ የኢኮኖሚ እድገት እንደሚመዘገብ ያመላከተ መሆኑን ጠቁመዋል ሲል ኢዜአ ዘግቧል።

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

# አባ መፍቅሬ የደን ገበሬ

ኢትዮጵያ የብዙ ደማቆች ሀገር መሆንዋ የታወቀ ቢሆንም ታሪካቸው በአግባቡ በወረቀት ላይ ተፅፎ የተመዘገበው የጥቂቶቹ ብቻ ነው። በተለያዩ የታሪክ አጋጣሚዎችና ባገኙአቸው ዕድሎች በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገር ዕውቀት ለመቅሰምና የበለጠ ግንዛቤ ለማግኘት የቻሉ አንዳንድ ኢትዮጵያውያን ያገኙትን ዕውቀት ለወገኖቻቸው ለማድረስና አዳዲስ አሠራርንና አስተሳሰብን በሕዝባችን መካከል ለማስረጽ፣ አብዝተው የደከሙና ሕይወታቸውን አሳልፈው እስከ መሰጠት የደረሱ ፋና ወጊ ምሁራን እንደ ነበሩ ይታወቃል።

ሀገራቸውን ከውጭ ወራሪና ጠላት በመከላከል አኩሪ ታሪክ የሠሩ፣ የሕዝባቸውን ደህንነትና አንድነት እንዲጠበቅ ለማድረግ መሥዋዕትነት የከፈሉና አንፀባራቂ ታሪክ የሠሩ ጥቂቶች አልበሩም። በደራሲነት፣ በሙዚቃ፣ በሥዕል፣ በስፖርት፣ በታሪክ፣ በሳይንስና በእምነት አስተምሮ፣ የኪነ ጥበብና የምርምር ሥራዎችም ኢትዮጵያን በዓለም የበለጠ እንድትታወቅ ያደረጉ ትናንትናም ዛሬም ደምቀው የሚታዩ ደማቅ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ብዙዎች ናቸው።

እነዚህ የሀገር ባለውለታዎች ሕይወታቸው ቢያልፍም ደማቅ ታሪካቸው ግን ዘወትር ሲወሳ ይኖራል። ስማቸው ከመቃብር በላይ ሆኖ ተተኪ ትውልድ ይማርበታል፤ ታዳጊዎች ይታነጹበታል፤ ሀገር ተረካቢዎች ዱካቸውን ተከትለው የነገዋን ኢትዮጵያ ይገነቡበታል።


ኢትዮጵያ በየዘመናቱ በሁሉም ዘርፍ ጀግኖችን ስታፈራ ቆይታለች። የዛሬው ጀግና ደግሞ ለየት ያለ ስብዕና ባለቤት የሆኑና በተለይም ለዛሬይቱ ኢትዮጵያ በእጅጉ አስፈላጊ የሆኑ ሰው ናቸው። የእኚህ ሰው የሕይወት ገጽታ እንዲህ ይነበባል።

የሁሉም አባት ናቸው። ሁሉም ልጆቻቸውም ናቸው ወጣት ፣ አዛውንት ፣ ህጻናት የክርስትና እምነት ተከታዮች ብቻም ሳይሆኑ የእስልምና እምነት ተከታይ የሆኑ በአጠቃላይ የደሴ ከተማ ሕዝብ ስለእሳቸው አባትነትና መልካምነት፤ የሥራ ትጋታቸውን ሰላም ወዳድ መሆናቸውን የተፈጥሮ ወዳጅ መሆናቸውን በአንድ ድምጽ ይመሰክሩላቸዋል። እኚህ ታላቅ አባት የሚጠሩትም ሕዝቡ ባወጣላቸው ስም ነው። ማንም ሰው ወላጆቻቸው ያወጡላቸውን መጠሪያ ስማቸውን አያውቀውም እሳቸውም ስለራሳቸው ማውራት የሚወዱ አይደሉም።

ነገር ግን ያገኟቸው ሁሉ አባ መፍቅሬ ይሏቸዋል፤ እሳቸውም ተቀብለውታል ። ሊቀ ትጉሃን አባ መፍቅሬ ሰብእ የእድሜያቸውን ከግማሽ በላይ ዛፎችን ሲተክሉ ደኖችን ሲያስጠብቁ አሳልፈዋል። በሥራዎቻቸው የሚደግፏቸውን ሰዎች በተፈጥሮ ላይ የሚያደርጉትን ጥቃት እና ጥፋት ምን ያህል ጉዳት ለው መሆኑን በማስተማር ሰዎች እንዲተባበሯቸው በማድረግ በቤተእምነት ቦታ እና በሌሎች በርካታ አካባቢዎች ዛፎችን ተክለዋል ደኖች እንዲጠበቁ አድርገዋል። እኚህ በደሴ ከተማ ሕዝብ ዘንድ እጅግ የሚወደዱት አባት በ96 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም ድካም አርፈዋል። በዛሬው የሕይወት ገጽታ አምዳችን እኚህን አባት ሕይወት የሚዘክር ከሰጧቸው ቃለመጠይቆች ፣ ስለእሳቸው ከተጻፉ እና ከተነገሩ ጥታሪኮች ይህንን ጥንክር አዘጋጅተናል።

“ደሴን በአራቱ ማዕዘን ስታዩአት አረንጓዴ ብትሆንባችሁ አትገረሙ፤ እርሳቸው ከአርባ ዓመት በላይ የለፉበት ነው። ለእርሳቸው ዛፍ የሚቆርጥ ቀርቶ ቅጠል የሚበጥስም የማርያም ጠላት ነው። አይከፈላቸውም፣ አልተመደቡም፣ ደብዳቤ የሰጣቸው የለም፣ እርሳቸው ግን 'የሀገሬ መራቆት የኔ መራቆት ነው' ብለው ደን ሲተክሉና ሲንከባከቡ ይኖራሉ” በማለት ዲያቆን ዳንኤል ክብረት በአንድ ፅሁፉ ስለ ጉምቱው የወሎ አባት ተምሳሌታዊ ሥብዕና አድናቆቱን ሰንዝሯል።

‹‹አባ መፍቅሬ ሰብዕ በደሴ ከተማ ከልጅነታችን ጀምሮ ስማቸውን እየሰማን ያደግን የሃይማኖት አባት ናቸው። ደሴ ተወልዶ እና አድጎ እሳቸውን የማያውቅ ይኖራል ማለት አይቻልም።›› በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ ትልቅ ቦታ የሚሰጣቸው ኡስታዝ



አቡበከር አህመድ በማህበራዊ ሚዲያ ገጻቸው ላይ ያሰፈሩት መልዕክት ነው።

አባ መፍቅሬ በጌምድር (ጎንደር) ክፍለሀገር ውስጥ በአገልግሎት በነበሩበት ጊዜ ደን ያለአግባብ ሲጨፈጨፍ በማየታቸው ከ 1943 ዓ.ም ጀምሮ 'ደን መጠበቅ አለበት' የሚል እሳቤ በመያዝ ዛፎችንም መትከል መጀመራቸውን ያስረዳሉ።

“የደን መጨፍጨፍ ለተለያዩ የተፈጥሮ ችግሮች ይዳርጋል። ዝናብ ይጠፋል፣ ድርቅ ይከሰታል፣ ሙቀት ይጨምራል። በመሆኑም ያለአግባብ ዛፍ የሚቆርጡትንና ደን የሚጨፈጭፉትን ከተግባራቸው እንዲቆጠቡ በተለያየ ጊዜ ትምህርት እሰጣለሁ። ከዚህ አልፈው በእኩይ ተግባራቸው የሚቀጥሉትንም የእግዚአብሔርን ቃል በመጥቀስ እገዝታቸዋለሁ” በማለት ለተፈጥሮ ያላቸውን ስስት ይናገራሉ።

የስማቸው ትርጓሜ እንደሚያስረዳው “መፍቅሬ ሰብእ” ማለት ሰውን የሚወድ በሰዎችም ዘንድ ተወዳጅ የሆነ ማለት ሲሆን ስማቸውንም ከተግባራቸው ተነስቶ ሕዝብ አወጣላቸው፣ እርሳቸውም ተቀበሉት። “መፍቅሬ ሰብ ማለት ሰው የሚወደው ማለት ሲሆን ዋናው ስምም የክርስቶስ ስም ሲሆን (ሰው ወዳጅ እግዚአብሔር) የሚል ትርጓሜም ስላለው ስያሜውን ልቀበለው ችያለሁ” በማለት አባ መፍቅሬ ሰብእ ይናገራሉ። ከትውልድ ሀገራቸው መቄት ወረዳ ወደ ደሴ ከተማ ከመጡ ጀምሮ ከቆሎ ተማሪነት ጀምሮ በሃይማኖት ትምህርት አሳልፈው በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች እየተዘዋወሩ አገልግለዋል።

አባ መፍቅሬ ሰብእ ለእጽዋት የተለየ ፍቅር አላቸው፣ ለደን የተለየ ቦታ ይሰጣሉ። የእድሜያቸውን ከግማሽ በላይ የተለያዩ ዛፎችን በመትከል ፣በመንከባከብ እና በመጠበቅ ሌሎችም እንዲንከባከቧቸው በማድረግ ያስተምራሉ።

በአንድ ወቅት በፋና ቴሌቪዥን በሰጡት ቃለ-መጠይቅ የደን ማስከበር ሥራቸውን በ1943 ዓ.ም በበጌ ምድር እንደጀመሩት ተናግረዋል። ደን ለሰው ልጆች ብቻም ሳይሆን በሥፍራው የሚኖሩ የዱር አራዊቶችን ብርቅዬ ተብለው የሚጠሩ እንስሳት ቁጥር እንዳይመናመን እንደሚያደርግ በተለያዩ መድረኮች ያስተምራሉ።

**“የአባ መፍቅሬ መገለጫ የሆነው ዋናው ባህሪያቸው ሰውን በሃይማኖቱና በማንነቱ ሳይመዝኑ በደስታውም ይሁን በኀዘኑ ጊዜ ፈጥነው ከጎኑ በመገኘት 'አይዞህ' የሚሉ አባት ናቸው**

ደን የሚጨፈጭፉ እና በተፈጥሮ ላይ ጉዳት የሚያደርሱ ሰዎችን ተፈጥሮን ብታጠፉ ዝናብ አታገኙም እያሉ ይናገራሉ። በሥራቸው ቁጭ ብለው የተማሩ የሰንበት ትምህርት ቤት አገልጋይ ህጻናትን የተለያዩ መጫዎችን በመስጠት እና በማበረታታት የተከሏቸውን ችግኞች እንዲያጠጡላቸው ያደርጋሉ ወጣቶችም ቢሆኑ በዚህ ተግባር ላይ እንዲሠማሩ ያደርጋሉ።

በሃይማኖት አባትነታቸው ብቻ ሳይሆን ለተፈጥሮ ባላቸው ቦታ የሚታወቁት አባ መፍቅሬ ከሚታወቁባቸው ሥራዎቻቸው ውስጥ አንደኛው የግሸን ደብረከርቤ የእምነት ሥፍራ የእምነቱ ተከታዮች ከተለያዩ ቦታዎች መጥተው እንዲገለግሉበት ያደረጉበት መንገድ ነው።

ግሸን ደብረ ከርቤ እንደ ዛሬው መንገዱ ሳይሠራና ለተጓዦች ምቹ ሳይሆን ብዙዎች ቦታው ላይ ተገኝተው የነፍስ ርሃባቸውን ለማስታገስ በምኞት ብቻ በሚኖሩበት ጊዜ የሕዝብን ስሜት ተረድተውና የቦታውን ታላቅነት ዓለም እንዲመሰክር፣ ወደሥፍራው መሄድን የተመኙም ምኞታቸው እንዲሰምር በ1973 ዓ.ም በወቅቱ ለነበሩ ባለሥልጣናት አባ መፍቅሬ ሃሳብ አቀረቡ።

ያቀረቡት ምክረ ሃሳብ አመኔታ በማግኘቱ እንኳን ለሰው ለዝንጀሮም ያስቸግራል የሚባለውን 17 ኪሎ ሜትር ተራራ መንገድ እንዲሠራበት በማድረግ እልፎችን ከምኞታቸው ጋር ያገናኙ፣ ታሪክ በደማቁ ከወርቅ መዝገብ ላይ ያሰፈራቸው፣ የግማደ መስቀሉ ማረፊያ ግሸን ደብረ ከርቤ ክብረ በዓል በመጣ ቁጥር ስማቸው አብሮ የሚነሳ አባ ፍቅሬ ሰብእ ናቸው።

ህጻን ዘላሊበላ በላሊበላ የሚገኙ ካህናት ያወጡላቸው ስያም ነው ‹‹አባ መፍቅሬ ›› ደግሞ በሥራዎቻቸው በተግባራቸው የአካባቢው ማህበረሰብ ሕዝብ ያወጣላቸው ስያሜ ነው። በወሎ እና አካባቢዋ ከሚከበሩ ኦርቶዶክስ ሃይማኖት ክብረ በዓላት አባ መፍቅሬን እነኚህን አባት ለይቶ ማየት በፍጹም አይቻልም።

አባ መፍቅሬ ሰብን በደሴ ከተማ የማያውቃቸው ሰው በፍጹም የለም። በክርስትና እምነት ተከታዮች ብቻም ሳይሆን በእስልምና እምነት ተከታዮች ዘንድ በአካባቢው ማህበረሰብ በደሴ ሕዝብ በእጅጉ የሚታወቁ እና የሚወደዱ የሃይማኖት አባት ብቻም ሳይሆን የሀገር ሽማግሌ አስታራቂ ፣ ልዩ የሀገር ፍቅር ያላቸው የተፈጥሮ ዘብ ናቸው። በዚህም ምክንያት አባ መፍቅሬ ሰብእ የሚል ስያሜ በጎንደር ከተማ ዞር አምባ ወጥቶላቸዋል።

የስማቸው ትርጓሜ እንደሚያስረዳው “መፍቅሬ ሰብእ” ማለት ሰውን የሚወድ በሰዎችም ዘንድ ተወዳጅ የሆነ ማለት ሲሆን ስማቸውንም ከተግባራቸው ተነስቶ ሕዝብ አወጣላቸው፣ እርሳቸውም ተቀበሉት። “መፍቅሬ ሰብ ማለት ሰው የሚወደው ማለት ሲሆን ዋናው ስምም የክርስቶስ ስም ሲሆን (ሰው ወዳጅ እግዚአብሔር) የሚል ትርጓሜም ስላለው ስያሜውን ልቀበለው ችያለሁ”።

በሀይቅ ገዳም በርካታ ዛፎችን ተክለዋል ። ልዩ የሚያደርጋቸውም የሚተክሏቸው የአየር ንብረት ለውጥ ላይ የራሳቸውን ተጽዕኖ ማሳረፍ ለውጥ ማምጣት የሚችሉ ተክሎችን እንዲሁም ሀገር በቀል እጽዋቶችን ነው።

ባህር ዛፍ ፣ ዋንዛ ፣ የሀበሻ ጽድ ፣ ዋርካ አባ መፍቅሬ ሰብእ የወሎ ዩኒቨርሲቲ ላበረከቱት አስተዋጽኦ በክብር የሸለማቸው ሲሆን የሚተክሏቸውን እጽዋቶች ልጆቼ ብለው ጭምር ይጠሯቸዋል። ከተለያዩ ቦታዎች ሽልማት እና እውቅና የተበረከተላቸው ሲሆን ወሎ ዩኒቨርሲቲ ለአበረከቱት አስተዋጽኦ እውቅና ሰጥቷቸዋል። በዚህም ‹‹አባ መፍቅሬ የደን ገበሬ››

ወደ ገጽ 7 ዞሯል

ማህበራዊ

# የሕይወት ገጽታ

## አባ መፍቅሬ...



ከገጽ 6 የዞረ

የሚል ስያሜም አላቸው።

በደሴ ከተማ የሚገኘውን የደሴ ቅዱስ ገብርኤል ቤተክርስቲያን በአካባቢው አጠጠራር ‹‹ዳግማዊ ላሊበላ›› እየተባለ የሚጠራ ሲሆን ህንጻ ሲሠራ ይህ ቤተክርስቲያን 18 ዓመታትን የፈጀ እና በብዙ አቅም ተሠርቶ እና ተገንብቶ ቀላል የማይባል ገንዘብን ከፈጀ በኋላ ባለመጠናቀቁ የህንጻ ቤተክርስቲያን አሠሪ ኮሚቴው የአቡነ አትናትዮስን እና የእሳቸውን አባ መፍቀሬ ሰብእ ፎቶ በጨረታ መልክ ለገበያ ቢያቀርቡት ከፍተኛ ገንዘብ ሊያገኙበት እንደሚችሉ በማሰብ ለአባ መፍቅሬ ሃሳብ ያቀርቡላቸዋል። አባ መፍቅሬ ይህንን ሃሳብ ሲሰሙ ለቤተክርስቲያ ከሆነ እንኳን ፎቶዬን እኔንም ሸጡኝ ብለው መናገራቸው የብዙዎች ትውስታ ነው።

አቶ ሰኢድ ሀሰን የደሴ ከተማ ነዋሪ ሲሆኑ አባ መፍቅሬ ሰብእን ከ30 ዓመት በላይ እንደሚያውቋቸው ገልጸው ስለ ማህበራዊ ተሳትፏቸው ምስክርነታቸውን ሲሰጡ "የአባ መፍቅሬ መገለጫ የሆነው ዋናው ባህሪያቸው ሰውን በሃይማኖቱና በማንነቱ ሳይመዝኑ በደስታውም ይሁን በኀዘኑ ጊዜ ፈጥነው ከጎኑ በመገኘት 'አይዞህ' የሚሉ አባት ናቸው። በሃይማኖቶችና በአማኙ መካከልም መተባበርና መከባበር እንዲኖር የሰሩት ተግባር ሁልጊዜም ከሰዎች ልብ ውስጥ እንዲኖሩ ያደርጋቸዋል" ይላሉ።

ዛሬ ላይ ግሸን ደብረ ከርቤ በዓመታዊ የንግሥ በዓሉ ላይ ሚሊዮኖች የሚገኙበት ስፍራ በመሆኑ ከሃይማኖታዊ ስፍራነቱ በተጨማሪ ለአካባቢው ማህበረሰብና ለዞኑ የገቢ ምንጭ ሆኖም እያገለገለም ይገኛል። ዲያቆን ናሁሰናይ ወልደሚካኤል ስለ አባ መፍቅሬ ሰብእ ተፈጥሮንና ልማት ወዳድነታቸውን ሲገልጽ "ማንኛውም ሰው አካባቢውን እንዲያለማ፣ ዛፎችን በመትከል ተፈጥሮን መንከባከብ እንዳለበትና የሀገር ቅርሶችን መጠበቅ እንደሚገባው በአውደምህረት ላይ ሳይቀር ትምህርት የሚሰጡ ድንቅ አባት ናቸው" ይላል።

"ዛፎቼ እንደሰው የማወራቸው ልጆቼም ጭምር ናቸው። ከእነርሱ ጋር በምሆን ሰዓት ሳልበላ ሁሉ እጠግባለሁ" የሚለው ንግግራቸው አባ መፍቅሬ ከተፈጥሮ ጋር ያላቸውን ጥልቅ ቁርኝት ማሳያ ነው።

**"ዛፎቼ እንደሰው የማወራቸው ልጆቼም ጭምር ናቸው። ከእነርሱ ጋር በምሆን ሰዓት ሳልበላ ሁሉ እጠግባለሁ" የሚለው ንግግራቸው አባ መፍቅሬ ከተፈጥሮ ጋር ያላቸውን ጥልቅ ቁርኝት ማሳያ ነው**

አባ መፍቅሬ የእድሜ ዘመናቸው ሙሉ ዛፍ በመትከል ተፈጥሮን መንከባከባቸውን፣ ለህብረተሰቡ ጠቃሚ የሆኑ በርካታ የልማት ሥራዎችን መሥራታቸውንም ለመዘከር "አባ መፍቀሬ፣ የደን ገበሬ/ አባ መፍቅሬ ሰብእ፣ የዛፎች ቤተሰብ" የሚል የአድናቆት መጠሪያ ስንኝ ማህበረሰቡ እስከማውጣት የደረሰ ሲሆን በተለያዩ ጊዜያትም በዞንና በክልል ደረጃ በርካታ የእውቅና ሽልማቶችን አግኝተዋል።

የደሴ ከተማ ማህበረሰብም ለአባ መፍቅሬ ሰብእ ያለውን ፍቅርና አክብሮት ለመግለጽ ባዋጣው ገንዘብ ወጪያቸውን ችሎ ሃይማኖታዊ ጸሎትና እንዲያደርሱና ጉብኝት እንዲያደርጉ ወደ ኢየሩሳሌምና ግብጽ ደርሰው እንዲመጡ አድርጓቸዋል።

የደሴ ከተማ በተለያየ ዘመን ካፈራቻቸው ታላላቅ ሰዎች መካከል ተፈጥሮን አብዝተው በመንከባከብ ችግኞችን በመትከል በርካታ ሰው ሰራሽ ደኖችን በመፍጠር የሚታወቁት ታላቁ አባት አባ መፍቅሬ ሰብእ አንዱ ናቸው።

አባ መፍቅሬ ሰብእ በማህበራዊ ኑሮ ላይ ያላቸው ንቁ ተሳትፎ በድፍን የደሴ ከተማ ሕዝብ ዘንድ ተወዳጅ ካደረጓቸው ተግባራት አንዱ ነው። የታመመ በመጠየቅ፣ የሞተን በመቅበር፣ ኀዘን በመድረስ፣ በደስታ ጊዜ ሰርግ ላይ በመገኘት፣ በበዓላት "እንኳን አደረሳችሁ" ለማለት ሰዎች ቤት በመሄድ፣ በወሎና በአካባቢው በሚከበሩ የኦርቶዶክስ ቤተክርስቲያን ሕዝባዊ በዓላት ላይ በማስተባበርና በማስተማር የሚያደርጓቸው ተሳትፎዎች ለሌሎች የኃይማኖት አባቶች እንደ ምሳሌ የሚጠቀሱ ናቸው።

ይህ ዘገባ ሲዘጋጅ አባ መፍቅሬ ሰብእ እድሜያቸው 80ዎቹ አጋማሽ ላይ የደረሰ መሆኑን የሚገልፁት አባ፣ የእድሜያቸውን 60ውን ዓመታት ከኃይማኖት ትምህርት ጎን ለጎን ዛፍ በመትከልና ተፈጥሮን በመንከባከብ እንዳሳለፉ ይናገራሉ። "ዛፎችን መትከል የጀመርኩት በቤተክርስቲያን ቅጥር ጊቢ ውስጥ ሲሆን ምክንያቱ ደግሞ ቤተክርስቲያን ውስጥ በሃይማኖታዊና በሌሎች ማህበራዊ ጉዳዮች ምክንያት ሕዝብ የሚሰባሰብበት ስፍራ በመሆኑ ማረፊያ ጥላ እንዲሆን በማሰብ ነው" ይላሉ።

በደሴ ከተማ የሚገኙትን አብዛኞቹን አብያተ ክርስቲያናት ማለትም የቅዱስ ገብርኤል ካቴድራል፣ ቁስቋም፣ አማኑኤል እና ኪዳነ ምህረት አብያተ ክርስትያናትን ካሳነጹት አባቶች መካከል አንዱ አባ መፍቅሬ ሰብ በመሆናቸው ምዕመኑ ሁልጊዜም ያስታውሳቸዋል። በሌላም ማህበረሰቡን በሚጠቅሙ የልማት ሥራዎች ላይ ነዋሪውን በማሳተፍና በማስተባበር ብዙ በጎ ተግባራትን ማከናወን የቻሉ አባት ናቸው።

መሪጌታ እዝራ በአምላኩ በልጅነት እድሜያቸው የቤተክህነት ትምህርት ለመከታተል በ1979 ዓ.ም ከትውልድ ሀገራቸው መቄት ወረዳ ወደ ደሴ ከተማ ከመጡ ጀምሮ ከቆሎ ተማሪነት ጊዜያቸው አንስቶ አባ መፍቅሬን የሚያውቋቸው ሲሆን ከእርሳቸው መለኮታዊ እውቀትን ከመማራቸው በተጨማሪ ችግኝ መትከልና የመንከባከብ ልምድ መውረሳቸውን ይናገራሉ።

"ልጅ ሆኜ የቆሎ ተማሪ እያለሁ እርሳቸው የሚተክሉትን ችግኝ ከወንዝ ውሃ እያመጣን በማጠጣት እናግዛቸው ነበር። ተግባሩን ልማድ አድርጌው አሁን ድረስ ችግኝ እተክላለሁ። አብዛኞቹን ደሴ ከተማ ውስጥ ያሉትን የቤተክርስቲያን አጸዶች ያሳመሩት እርሳቸው ሲሆኑ ለዚህም የቅዱስ ገብርኤል ካቴድራል አንዱ ማሳያ ነው" ይላሉ መሪጌታ እዝራ።

ዲያቆን ዳንኤል ክብረት በአንድ ወቅት ስለአባ መፍቅሬ ሰብእ "የተሸጡት አባት" በሚል ርዕስ በአዲስ ጉዳይ መጽሄት ላይ ባሳተመው ጽሁፉ ስለ አባ መፍቅሬ ሰብእ የስብዕና ከፍታ እና የሕዝብ ፍቅር እንዲህ በማለት ምስክርነቱን ሰጥቷል፤

"ለእርሳቸው ዘርና ሃይማኖት ሰውን ለመርዳት መመዘኛዎች አይደሉም። ሰውነት ብቻ ይበቃቸዋል። ይህ ርዳታቸው ከመከራ ያወጣቸው፣ ከችግር የታደጋቸውና ሕይወታቸውን ያቀናላቸው ሰዎች ስለ እኒህ አባት ሲያወሩ ከማያቋርጥ ዕንባ ጋር ነው። አንዳንዶች እንዲያውም ከንግግር ይልቅ እርሳቸውን እያሰቡ ዝም ብለው በማልቀስ ይገልጧቸዋል። መቼም ለአንዳንዱ አብዝቶ አይደል የሚሰጠው። እርሳቸው የአካባቢ ጥበቃ አርበኛም ናቸው።

ዳንኤል በፅሁፉ ስለ አባ መፍቅሬ ሰብዕ የረዥም ዓመታት የተፈጥሮ ጥበቃ ሥራ ውጤታማነትን ከመግለፁ ባሻገር የአባ መፍቅሬን የአካልና የመንፈስ ጥንካሬ በማድነቅ፤ በራስ ተነሳሽነት ለሀገር ስላደረጉት ትልቅ ተግባር እንዲህ ይላል፡-

"በዚህ የእርጅና እድሜያቸው እንኳን መኮትኮቻና መቆፈሪያ፣ አካፋና ባሬላ ይዘው በደሴ ተራሮች ላይ ዛፍ ሲተክሉ ይውላሉ። ደሴን በአራቱ ማዕዘን ስታዩዋት አረንጓዴ ብትሆንባችሁ አትገረሙ፤ እርሳቸው ከአርባ ዓመት በላይ የለፉበት ነው። ለእርሳቸው ዛፍ የሚቆርጥ ቀርቶ ቅጠል የሚበጥስም የማርያም ጠላት ነው። አይከፈላቸውም፣ አልተመደቡም፣ ደብዳቤ የሰጣቸው የለም፣ እርሳቸው ግን 'የሀገሬ መራቆት የኔ መራቆት ነው' ብለው ደን ሲተክሉና ሲንከባከቡ ይኖራሉ።"

አባ መፍቅሬ ሰብእ ከተከሏቸው ደኖች መካከል ከደሴ ከተማ 35 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ የሚገኘውና በዘጠነኛው ክፍለ ዘመን እንደተመሠረተ የሚነገርለት የሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም ቅጥር ጊቢ አይነተኛ ማሳያ ነው። ገዳሙ ከተለያዩ የኢትዮጵያ ክፍሎች ለሚመጡ ተማሪዎች ሃይማኖታዊ ትምህርት ይሰጥበት የነበረ ሲሆን አንዳንድ ምሁራንና አበው "የመካከለኛው ዘመን የኢትዮጵያ ሥነ መለኮት ዩኒቨርሲቲ" በማለት ይገልፁታል። አባ መፍቅሬ ሰብእ የሐይቅ እስጢፋኖስ ገዳም ቅጥር ግቢን የተለያዩ ሀገር በቀል ዛፎችን በመትከል አካባቢውን ባላበሱት ግርማ ሞገስ፣ በጣም ማራኪ፣ የዓይን ማረፊያና የመንፈስ ምግብ ብሎም የቱሪስት መስህብ መሆኑ ለታላቅ ተግባራቸው ቋሚ ምስክር ሆኗል።

"የደሴ ከተማ ሕዝብ ከሕዝበ ክርስቲያኑ ባልተናነሰ ሙስሊሙ ማህበረሰብም ለኔ ያለውን ፍቅርና አክብሮት ይገልጽልኛል። ያገኙኝ ሁሉ 'አላህ ረዥም እድሜ ያኑርህ' እያሉ ይመርቁኛል" በማለት የከተማውን ነዋሪ ስለሚለግሳቸው ፍቅር እና አክብሮት ይናገራሉ።

በደሴ ከተማ ሕዝብ ዘንድ በእጅጉ የሚታወቁት እኚህ አባት ለብዙዎች ምሳሌ መሆን የሚችል ሥራን እስከ እርጅና እድሜቻው ድረስ ሠርተው አባ መፍቀሬ ሰብእ ባደረባቸው ህመም በ96 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም ድካም አርፈዋል። ለሀገር የዋሉት ውለታ እና የአባትነት ፍቅራቸውም በቅርበት ለሚያቋቸው የማይጠገብ ተነግሮ የማያልቅ ሲሆን እንደሀገር ያላቸው እውቅና እና የተሰጣቸው ቦታ እምብዛም አልተጠቀምንባቸውም በሚል የሚያስቆጭ መሆኑን ይገልጻሉ።

በአጠቃላይ ሰውና ሸክላ ተሰባሪ ነው። ዋናው ነገር የማይሰበር ስም ትቶ ማለፍ ነው። አባ መፍቀሬ ይህንን ልዕልና ከተጎናጸፉ ጥቂት ሰዎች ውስጥ አንዱ ናቸው። በኖሩባቸው ዓመታት ሰውን በሰውነቱ እንጂ በሃይማኖቱ እና ብሄሩ ሳይለዩ ማድረግ የሚገባቸውን ያደረጉ የታላቅ ስብዕና ባለቤት ናቸው።

አሁን እንደሀገር የተጠናወተንን በሽታ አራግፈው የጣሉና ለብዙዎችም በአርአያነት የሚጠቀሱ ስነበሩ። ለእኒህ የገዘፈ ሥብዕና ለነበራቸው አባታችውን ነፍስሄር በማለት ሁላችንም የሳቸውን ሥብዕና የምንላበስበትን ጸጋ እና አቅም ይስጠኝ በማለት ጽሁፌን አጠቃልላለሁ።

# የአስጎብኚ ድርጅቶች የቱሪዝም ዘርፉ ሚና

**ዳግም ከበደ**

የቱሪዝም ዘርፍ በኢኮኖሚ ላይ የሚኖረውን ድርሻ ለማሳደግ ነባርና አዳዲስ የመዳረሻ ልማቶችን ማካሄድ፣ የመስህብ ሀብቶችን ማስተዋወቅ፣ ዘመናዊ ቴክኖሎጂን መጠቀም አስፈላጊ መሆኑን የዘርፉ ባለሙያዎች ይናገራሉ። ለዘርፉ የተሰጠውን ትኩረት የሚመጥን መዋቅራዊ አደረጃጀትና የባለድርሻ አካላት የተቀናጀ አሠራር መዘርጋትም ሌላው ቀዳሚ ተግባር መሆን እንዳለበትም ይጠቁማሉ። ነባራዊ ሁኔታን ያማከሉ ፖሊሲና የሕግ ማሻሻያዎች ማድረግም እንዲሁ ለውጤታማነቱ ቀዳሚውን ድርሻ ከሚወጡ ተግባራት መካከል መሆናቸውንም ባለሙያዎቹ ያስረዳሉ።

ከላይ ከተጠቀሱት መሠረታውያን ባሻገር ቱሪዝም በሀገሪቱ ኢኮኖሚ ላይ ተጨባጭ ለውጥ እንዲያመጣ ለማድረግ የግሉ ዘርፍ ሚና ተኪ እንደሌለውም ይገለጻል። በተለይ የሆስፒታሊቲ፣ የትራንስፖርትና የአስጎብኚ ባለሙያዎችና ቱር ኦፕሬተሮች ሚና ከፍተኛ ስለመሆኑም ይጠቁማል። መንግሥት የመስህብ ሥፍራዎችን የመለየት፣ የማልማት፣ የመጠበቅና የጎብኚዎችን ደህንነት የማረጋገጥ ድርሻን ይውሰድ እንጂ፤ ከግል ዘርፉ ጋር ካልተቀናጀ የሚፈለገው ውጤት ሊመጣ አይችልም።

በዘርፉ የዓለም አቀፍ ቱሪስት ፍሰት ከፍተኛ እንዲሆን አስጎብኚ ድርጅቶችና ባለሙያዎች (tour operators and professionals) ከፍተኛ ድርሻ እንዳላቸው ይገለፃል። አስጎብኚ ድርጅቶች የኢትዮጵያን የባህል፣ የታሪክ፣ የተፈጥሮና ሌሎች የቱሪዝም መስህቦችን ለጎብኚዎች በማስተዋወቅ ከፍተኛ የቱሪስት ቁጥር ወደ ኢትዮጵያ እንዲገባ፤ ቆይታቸውንም በማራዘም፣ የሀገሪቱን ገፅታና ኢኮኖሚያዊ አቅም እንዲያሳድግ የማድረግ ኃላፊነትን እንደሚወጡ ይገለፃል።

አስጎብኚ ድርጅቶችና ባለሙያዎች በተለይ ቱሪስቶች የኢትዮጵያን የቱሪስት መዳረሻዎች ለመጎብኘት በሚመጡበት ወቅት የጉዞ እቅድ በማውጣት፣ የሚያርፉበትን ሆቴል፣ የሚጎበኟቸውን መስህቦች በማመቻቸት፣ በቆይታቸው የተሻለ ልምድና ተዝናኖትን አግኝተው ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ በማድረግ በኩል ብዙ መሥራት ይጠበቅባቸዋል።

መንግሥት የግል ባለሀብቶችና ተቋማት በሆቴል (በቱሪዝም ኢንቨስትመንት)፣ በገልግሎት ዘርፍ፣ በአስጎብኚ ድርጅቶች፣ በሌሎችም ንኡስ የቱሪዝም ዘርፎች ላይ እንዲሰማሩ እያበረታታ ይገኛል። ከእነዚህ ውስጥ አስጎብኚ ድርጅቶች በቀዳሚነት ይጠቀሳሉ። ይህም ድርጅቶቹና በጉብኘት መሪነት የሚያገለግሉት ባለሙያዎች ውጤታማነት ለዘርፉ ዘላቂ እድገት ቁልፍ ሚና እንደሚጫወትም ይታመናል።

ንብረት አደም መሀመድ የሀመር ላንድ የኢትዮጵያ አስጎብኚ ድርጅት ባለቤትና ማኔጂንግ ዳይሬክተር ነው። የዝግጅት ክፍላችን በመስከረም ወር መጨረሻ ላይ በተካሄደው የኦሮሚያ ቱሪዝም ሳምንት ላይ በተገኘበት ወቅት በኢትዮጵያ ቱሪዝም ዘርፍ ላይ ድርጅቱ እየሠራ ስላለው ሥራ አነጋግሮት ነበር። እርሱ እንደሚለው፤ ሀመር ላንድ ላለፉት 11 ዓመታት የመስህብ ሀብቶቹን ለዓለም አቀፍና ለሀገር ውስጥ ቱሪስቶች ሲያስጎበኝ ቆይቷል። በዋናነትም በደቡባዊው ኢትዮጵያ በጅንካና በኦሞ ሸለቆ አካባቢ የሚገኙ መዳረሻዎችን ሲያስተዋውቅ ቆይቷል። በአሁኑ ሰዓት በአዲስ አበባ ቢሮ ከፍቶ በሁሉም የኢትዮጵያ አካባቢዎች ተደራሽ ለመሆን እየሠራ ይገኛል።

‹‹በውጭ ሀገር ቱሪስቶች ላይ ዋና ትኩረታችንን አድርገን እየሠራን ነው›› የሚለው ማኔጂንግ ዳይሬክተሩ፣ ቱሪስቶቹን ወደ ኢትዮጵያ ለማምጣት በድርጅቱ ዌብ ሳይት፣ በቱሪስት አድቫይዘር፣ በአውደርዕይ እንዲሁም በአጋርነት ከሚሰሩ የውጭ ኩባንያዎች ጋር ድርጅቱ ያደረገውን ስምምነት እንደሚጠቀም ያስረዳል።

ማህበራዊ ሚዲያ (በኢንስታግራም፣ በቲውተር፣ ፌስቡክና በመሳሰሉት ገጾች) የኢትዮጵያን የመስህብ ሥፍራዎች በማስተዋወቅ እንዲሁም ድርጅቱ ልዩ ጥቅሎችን በማዘጋጀት ቱሪስቶቹ ሀገሪቱን



እንዲጎበኙና ቆይታቸውን አራዝመው እንዲሄዱ እንደሚያመቻች ይገልፃል። ይህ መሆኑ የሀገሪቱን ኢኮኖሚን ከማሳደጉም ባሻገር መዳረሻው አካባቢ ለሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች የሥራ እድል ፈጠራ አስተዋጽኦ እንዳለው ይገልፃል።

ከ 14 ዓመቱ ጀምሮ በጅንካ የአካባቢውን ሀብቶች በማስተዋወቅ ከቱሪስቶች ጋር የመሥራት ልምድ እንዳዳበረ የሚናገረው ማኔጂንግ ዳይሬክተሩ ንብረት፤ የተወለደበት አካባቢ በባህል የበለፀገና የጎብኚዎችን ቀልብ የሚስብ መሆኑ በይበልጥ ከሙያው ጋር እንዳስተዋወቀው ይናገራል። በኢትዮጵያ ሁሉም አካባቢ መሰል የባህል፣ የተፈጥሮ፣ የቅርስ እና አርኪዮሎጂካል መንደሮች መኖራቸውን ጠቅሶ፣ ሁሉም የድርሻውን መወጣት ከቻሉና ዘርፉ እንዲያድግ በቅንጅት ከተሠራ የቱሪስት ፍሰቱን ማሳደግ እንደሚቻል አስታውቋል።

‹‹ለቱሪዝም እድገት እንዲሁም ለቱሪስት ፍሰቱ መጨመር በዋናነት ሰላም አስፈላጊ ነው›› የሚለው ማኔጂንግ ዳይሬክተሩ፣ ዓለም አቀፍ ቱሪስቱን ለመሳብ የቱሪዝም ሀብቶቹን ማስተዋወቅና ተወዳዳሪ ማድረግ አስፈላጊ ቢሆንም ቀዳሚው ጉዳይ ግን ሰላምና ደህንነትን ማስፈን ነው›› ሲል ያስገንዝባል:: ይህንን ማድረግ ከተቻለ አፍሪካ ውስጥ ካሉ ተመራጭ የቱሪስት መዳረሻዎች ውስጥ ኢትዮጵያን በቀዳሚነት ማሰለፍ የሚያስችል አቅም እንዳለ ገልጿል።

እንደ ማኔጂንግ ዳይሬክተሩ ገለፃ፤ የኢትዮጵያ ቱሪዝም ከዋና ዋና የኢኮኖሚ ምሰሶዎች (እንደ ግብርናና ማኑፋክቸሪንግ) ካሉት አንዱ መሆን የቻለና በኢኮኖሚው ላይ ከፍተኛ ተፅእኖ መፍጠርም የሚችል ኢንዱስትሪ ነው። ይህንን በሚገባ ለመጠቀም የቱሪዝም መሠረተ ልማት ማሟላት፣ ሰላምና ደህንነት ማስፈን እንዲሁም በሆስፒታሊቲ ዘርፉ ላይ የተማሩ ባለሙያዎችን ማሠማራት እንደሚያስፈልግ አመልክቷል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የኮቪድ ወረርሽኝን እንዲሁም በአንዳንድ አካባቢዎች የተከሰቱ አለመረጋጋቶችን ተከትሎ ጥቂት የማይባሉ የአስጎብኚ ደርጅቶች ዘርፍ እየቀየሩ እንደሚገኙ የሚገልፀው ማኔጂንግ ዳይሬክተሩ፤ ሀመር ላንድ እና ሌሎች መሰል የአስጎብኚ ድርጅቶች ግን የቱሪዝም ዘርፉ ያለውን መልካም አድል እና በመንግሥት የተሰጠውን ከፍተኛ ትኩረት በመመልከት አሁንም ድረስ ድርጅቶቻቸውን አጠናክረው መቀጠላቸውን ይገልፃሉ።

ደቡባዊው የኢትዮጵያ ክፍል ባህላዊ ሀብቶች በስፋት የሚገኙበት እንደመሆኑ መጠን የሀመር ላንድ አስጎብኚ ድርጅትም ዋናው ትኩረቱን በባህል ቱሪዝም ላይ አድርጓል ሲል የሚናገረው ንብረት ፤ በሌሎችም የተፈጥሮና የታሪክ መዳረሻዎች ላይ ቱሪስቶችን በመውሰድ የኢትዮጵያን ሀብቶች እንደሚያስተዋውቅ ያስረዳል።

ማኔጂንግ ዳይሬክተሩ ከአስጎብኚነት ባሻገርም የፎቶግራፍ ባለሙያ መሆኑን ጠቅሶ፣ ላለፉት ስድስት ዓመታት ከታዋቂው የፎቶግራፍ ባለሙያ ጆዊ ላውረንስ ጋር በመተባበር ‹‹ኢትዮጵያ›› የሚል ስያሜ ያለው የፎቶግራፍ መፅሀፍ ማሳተሙን ይገልጻል። ይህ መፅሀፍ በአማዞን ከፍተኛ ሽያጭ እያስመዘገቡ ካሉ የፎቶ መፅሀፎች ውስጥ አንዱ መሆኑንም ጠቅሶ፣ ይህ ሥራቸውን የቱሪዝም ዘርፉ ያለውን አቅም፣ የኢትዮጵያን ሁለንተናዊ ውበትና መስህብ ለማሳየት እንደተጠቀሙበትና፤ ተጨማሪ አቅም አንደሚሆን ሙሉ እምነት የጣለበት መሆኑን ተናግሯል።

‹‹የኢትዮጵያን ቱሪዝም አሁን ካለው በተሻለ ማሳደግ ይገባል›› የሚል እምነት ያለው ማኔጂንግ ዳይሬክተሩ፤ በኮቪድ ወረርሽኝና በአንዳንድ አካባቢዎች አሁንም ድረስ ባለው አለመረጋጋት እየተፈጠረ ያለውን ጫና ለመቀነስ መንግሥትና ሁሉም ባለድርሻ አካላት በቅንጅት ሊሠሩ እንደሚገባ አመልክቷል። እንደ አስጎብኚ ድርጅትም ኢትዮጵያ ያሏትን ሀብቶች በማስተዋወቅ ከቱሪስት የሚገኘውን ኢኮኖሚያዊ ጥቅም መጠቀም እንዲቻል የግል ድርሻውን እንደሚወጣም አስረድቷል።

ሃይማኖት ዘርዓይ የሰሜን ኢኮ ቱሪስት አስጎብኚ ድርጅት የማርኬቲንግ ባለሙያ ነች። ሰሜን ኢኮ ቱሪስት በዋናነት ተፈጥሮን መሠረት በማድረግ በሰሜኑ የኢትዮጵያ ክፍል ያሉ የቱሪዝም ሀብቶችን ለቱሪስቶች በማስጎብኘት ይታወቃል። የአየር ንብረት እና የአካባቢ ጥበቃ ተቆርቋሪ በመሆንም የተፈጥሮ ቱሪዝም በኢትዮጵያ ሰፊ ድርሻ እንዲኖረው እየሠራ መሆኑን የማርኬቲንግ ባለሙያዋ ሃይማኖት ትናገራለች።

ዓለም አቀፍ ቱሪስቱ የኢትዮጵያን የተፈጥሮ ሀብቶች እና መልከዓ ምድር ለመጎብኘት ፍላጎት እንዲኖረው ሰሜን ኢኮ ቱሪዝም እየሠራ መሆኑን የምትናገረው የማርኬቲንግ ባለሙያዋ፤ ጎብኚዎች በተፈጥሮ አካባቢዎች ሲገኙ ምንም አይነት ተፈጥሯዊ ያልሆኑ በአድ ነገሮች እንዲጠቀሙ ድርጅታቸው እንደማይፈቅድ አስታውቃለች።

‹‹በኢትዮጵያ ቱሪዝም እድገት ላይ በጎ ተፅእኖ ለመፍጠር እየሠራን ነው›› የምትለው የሰሜን ኦኮ ቱሪስት አስጎብኚ ድርጅት ማርኬቲንግ ባለሙያዋ ሃይማኖት፤ በዓለም አቀፍ መድረክ ኢትዮጵያ ለአየር ንብረትና ለአካባቢ ጥበቃ ልዩ ትኩረት የምትሰጥ ሀገር ስለመሆኗ ድርጅቷ አጉልቶ ለማሳየት እና ገፅታዋን ለመገንባት እየሠራ መሆኑንም ጠቅሳለች። በዚህም ተፈጥሮ የሚወዱና የሚንከባከቡ ቱሪስቶች ላይ ልዩ ተኩረት አድርገው እንደሚሠሩ ትገልፃለች።

እሷ እንደምትለው፤ በሰሜን ኢኮ ቱሪስት አስጎብኚ ድርጅት አማካኝነት በርካታ ቱሪስቶች ወደ ኢትዮጵያ ይገባሉ፤ አስጎብኚ ድርጅቱ እነዚህ ቱሪስተቶች በጉዞ ላይም ይሁን በማረፊያ ቦታቸው የፕላስቲክ ኮዳ ባለመጠቀም፣ ተፈጥሯዊ ምርቶችን በማበረታታት፣ ለአየር ብክለት ምክንያት ሊሆኑ የማይችሉ ቁሳቁስን በመያዝ መስህብ ሥፍራዎችን እንዲጎበኙ ያደርጋል:: ጎብኚዎች ለኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ከሚያበረክቱት አስተዋጽኦ ባሻገር ለመዳረሻ ሥፍራዎች ጥበቃ የሚኖራቸውን ደርሻ ማሳደግ ይገባል ስትል ገልጻ፣ ይህን ማድረግ ከተቻለ ዘላቂና ጠንካራ የቱሪዝም ዘርፍ መገንባት እንደሚቻል አስታውቃለች::

እንደ ማርኬቲንግ ባለሙያዋ ገለፃ፤ አስጎብኚ ድርጅቶች ለኢትዮጵያ ቱሪዝም እድገት ከፍተኛ ድርሻ አላቸው። ቱሪስቶች ወደ ኢትዮጵያ በብዛት እንዲገቡ፣ ደረጃውን የጠበቀ መስተንግዶ እንዲያገኙና በብቁ ባለሙያ መዳረሻዎችን እንዲጎበኙ የድርጅቶቹ አቅም ማደግ ይገባዋል። ለዚህም መንግሥት ልዩ ልዩ ማበረታቻዎችን በማድረግና በቅንጅት በመሥራት ሊደግፋቸው ይገባል። ይህንን በዘላቂነት ማድረግ ከተቻለ በቱሪዝም ዘርፉ እንዲመጣ ለሚታሰበው ለውጥ የአስጎብኚ ደርጅቶች የጀርባ አጥንት መሆን ይችላሉ።

ሰሜን ኢኮ ቱሪስት አስጎብኚ ደርጅት ከተመሠረተ ዘጠኝ ዓመታትን አስቆጥሯል:: በእነዚህ ጊዜያት የሰሜኑን የኢትዮጵያ ክፍል ጨምሮ በሁሉም የኢትዮጵያ ክፍሎች የሚገኙ የቱሪስት መዳረሻዎችን ለቱሪስቶች ሲያስጎበኝ ቆይቷል:: ይሁን እንጂ የኮሮና ወረርሺኝና፣ በአገሪቱ የነበረው አለመረጋጋት ዘርፉ ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ፈጥሯል፤ ይህን ተከትሎም የቱሪስቱ ቁጥር ቀንሷል።

ደርጅቱ እነዚህን ችግሮች ተቋቁሞ ኢትዮጵያን ማስተዋወቁን መቀጠሉን ተናግራ፣ አሁንም ድረስ የቀጠለው አለመረጋጋትና የሰላም መደፍረስ መፍትሄ ሲያገኝ አሁን ካለውም በተሻለ መሥራት እንደሚችሉ አስታውቃለች።

በኢትዮጵያ አዳዲስ የቱሪስት መዳረሻዎች እየተገነቡ ስለመሆናቸውም ሃይማኖት ጠቅሳ፣ መስህቦቹ ዓለም አቀፍ ቱሪስቶች በብዛት እንዲመጡ ለማድረግ የበኩላቸውን አስተዋጽኦ እንደሚያደርጉም ትገልፃለች። ድርጅታቸው ለቱሪስቶች የሚያዘጋጀውን የጉብኝት እቅድ ለማስፋት የተገነቡትና እየተገነቡ የሚገኙ መዳረሻዎች ተጨማሪ አቅም እንደሚፈጥርላቸውም ታስረዳለች።

ቱሪዝም በኢትዮጵያ ኢኮኖሚ ላይ ልዩ ድርሻ እንዲኖረው መዳረሻዎችን ማልማት፣ ማስተዋወቅና ነባሮቹን ከጉዳት መጠበቅ አስፈላጊ መሆኑን አመልክታ፣ ከሁሉም በላይ ግን ሰላም ለቱሪስቶች ደህንነት አስፈላጊ እንደሆነ ጠቁማለች። በመሆኑም ሁሉም ኢትዮጵያዊ አሁን ያለው አለመረጋጋት እንዲሰክንና ሰላም እንዲፈጠር መሥራት እንደሚገባው አስገንዝባለች።

ይህንን ማድረግ ከተቻለ የኢትዮጵያ የቱሪዝም ሀብቶች ከበቂ በላይ መሆናቸውን ጠቅሳለች። እንደ አስጎብኚ ድርጅት የኢትዮጵያ ሰላም እንዲመለስ፣ መልካም ገፅታዋ ተጠብቆ እንዲቆይ ለማስቻል ድርጅቱ ከመንግሥትና ከሌሎች መሰል ድርጅቶች ጋር በትብብር እንደሚሠራም አረጋግጣለች።

**እንደ መውጫ**

አስጎብኚ ድርጅቶችና የጉብኝት መሪዎች የቱሪዝም ዘርፉ የጀርባ አጥንት መሆናቸው ይነገራል። ድርጅቶቹ የአንድ ሀገር ባህል፣ ተፈጥሮ፣ ታሪክና ቅርስ በቱሪስቶች አይን ውስጥ እንዲገባ ዋናውን ድርሻ ይወስዳሉ። የጉብኝት እቅድ መንደፍ፣ ማረፊያ ቦታዎችን ማዘጋጀት፣ ጎብኚው ስለ መስህቦቹ በቂና ትክክለኛ መረጃ እንዲያገኝ ማድረግ፣ ቱሪስቱ ምቾት ተሰምቶት ቆይታውን እንዲያራዝም ተፅእኖ መፍጠር የእነዚህ አስጎብኚ ድርጅቶችና የጉብኝት መሪዎች (Tour Guide) ሃላፊነት ነው።

ለዚህም ነው መንግሥት መዳረሻዎችን ከማልማት፣ ሰላምና መረጋጋትን ከማስፈን፣ ታሪካዊና ተፈጥሯዊ ቦታዎችን ከመጠበቅ ባሻገር ኢንዱስትሪውን ከሚያንቀሳቅሱ መሰል ድርጅቶች ጋር በቅርበት መሥራት እንዳለበት የሚታመነው። መንግሥት በተለይ አቅማቸው እንዲጎለብት፣ መዋቅራዊ አደረጃጀታቸው ጠንካራ እንዲሆን ክትትልና ድጋፍ ማድረግ እንዳለበት የዘርፉ ምሁራን ምክረ ሃሳብ ይሰጣሉ።

ስፖርት እና መዝናኛ

# ሳምንቱን በታሪክ

# ሁልጊዜም አዲስ የሚሆኑት፤ ሀዲስ አለማየሁ

ዋስልኝ አየለ

ሀዲስ አለማየሁ በዚህ ዓመት፤ ታሪክ ብቻ ሳይሆኑ ዜና ጭምር ሆነዋል። ፍቅር እስከ መቃብር በፊልም ተሠርቶ በኢትዮጵያ ቴሌቭዥን መታየት ከጀመረበት ዕለት ወዲህ እንደ አዲስ አጀንዳ ሆኗል። ከ115 ዓመታት በፊት በዚህ ሳምንት ጥቅምት 7 ቀን 1902 ዓ.ም የተወለዱትና የዚህ ድንቅ መጽሐፍ ጸሐፊ የሆኑት ሀዲስ አለማየሁ የዚህ ሳምንት ባለታሪካችን ናቸው።

ሀዲስ አለማየሁ በሥነ ጽሑፉ ዘርፍ ብዙ ተብሎላቸዋል። ሀዲስ ግን ከሥነ ጽሑፍ ሥራዎቻቸው የበለጠ የኖሩት በፖለቲካ ሥራ ላይ ነው። መጽሐፎቻቸውም የፖለቲካ ተሳትፏቸው ውጤቶች ናቸው። የድርሰት ሥራዎቻቸውን ብቻ ሳይሆን የፖለቲካ ሕይወታቸውንም እንመለከታለን።

ሀዲስ ከአለቃ አለማየሁ ሰለሞን እና ከወይዘሮ ደስታ ዓለሙ በ1902 ዓ.ም ጎጃም ውስጥ ተወለደ። አያቱ (የእናቱ አባት) አለቃ ዓለሙ ስዩም በእንዶዳም ኪዳነ ምህረት ገዳም የዜማ መምህር ስለነበሩ ስድስት ዓመት ሲሞላው የግዕዝ ፊደሎችን ማጥናት ጀመረ። ከእንዶዳም ኪዳነ ምህረት በተጨማሪ በደብረ ኤልያስ፣ በደብረ ወርቅና በዲማ ጊዮርጊስ ገዳማት ተዘዋውሮ የድጓ፣ የቅኔና የመጻሕፍት ቤት (ትርጓሜ) ትምህርቶችን ተማረ። በትምህርቱም ከጓደኞቹ ሁሉ የላቀ ነበር። በ1918 ዓ.ም ሐዲስና ሌሎች ጓደኞቹ ከመምህራቸው መሪጌታ በላይ ጋር በመሆን ወደ አዲስ አበባ አቀኑ።

አዲስ አበባ ደርሰው ጥቂት ጊዜያትን ካሳለፉ በኋላ አቶ አያሌው ንጉሤ ከተባሉና በስዊድን ሚሲዮን ትምህርት ቤት ያስተምሩ ከነበሩ ግለሰብ ጋር ተዋወቁ። አቶ አያሌውም ሀዲስና ጓደኞቹ ወደ ስዊድን ሚሲዮን ትምህርት ቤት ገብተው ዘመናዊ ትምህርት እንዲማሩ መከሯቸው። ሀዲስ ትምህርት ቤቱ ሃይማኖቴን ሊያስለውጠኝ ይችላል ብሎ በመፍራቱ ጥቂት አመነታ። በመጨረሻ ግን ወደ ስዊድን ሚሲዮን ትምህርት ቤት ገብቶ ትምህርቱን ጀመረ። በሂደትም የዘመናዊ ትምህርትን ጥቅም በማወቁ የመንግሥት ትምህርት ቤት መግባት እንዳለበት ወስኖ ተፈሪ መኮንን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤትን ተቀላቀለ። ከራስ ኃይሉ ተክለሃይማኖት ግምጃ ቤት ባገኘው ወርሃዊ የገንዘብ ድጋፍም ከሦስተኛ እስከ ስድስተኛ ክፍል ድረስ ያለውን ትምህርቱን በተፈሪ መኮንን የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤት ተከታተለ።

በወቅቱ በትምህርት ቤቱ ውስጥ አመፅ ተቀስቅሶ ነበር፡ « ... የአመፁ ጠንሳሾች በእድሜያቸው በሰል ያሉት ተማሪዎች ናቸው ... » ተብሎ በመታመኑ እድሜያቸው ከ18 ዓመት በላይ የሆኑ ተማሪዎች ማደሪያቸው ከትምህርት ቤቱ ውጭ ሆኖ እንዲማሩ ተወሰነ። ይህ ውሳኔ አዲስ አበባ ውስጥ ቤተሰብና የቅርብ ዘመድ ለሌላቸው የትምህርት ቤቱ ተማሪዎች አስደንጋጭ ነበር። ሀዲስ አዲስ አበባ ውስጥ ቤተሰብም ሆነ የቅርብ ዘመድ ስላልነበረው ትምህርቱን ለማቋረጥ ተገደደ።

በወቅቱ በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ይሰጥ የነበረውን የመምህርነት ሥልጠና ወስዶ በስዊድን ሚሲዮን ትምህርት ቤት ማስተማር ጀመረ። ከዘጠኝ ወራት የመምህርነት ሥራ በኋላ ዳንግላ አካባቢ በነበረው የብሪታኒያ ቆንስላ ውስጥ እንዲሠራ ተመደበ። ዳንግላ አካባቢ የነበረው የብሪታኒያ ቆንስላ ከተዘጋ በኋላ ሀዲስ በአካባቢው የነበረው ጉምሩክ ተቆጣጣሪ ሆኖ መሥራት ጀመረ። በዚህ ሥራው ላይ ብዙም አልቆየም። በወቅቱ በአካባቢው የባሪያ ንግድ ይካሄድ ስለነበር የባሪያ ንግድ እንዲቆም የኢትዮጵያ ንጉሠ ነገሥት መንግሥት ያወጣቸውን ድንጋጌዎችን የማስፈጸምና የመከታተል ኃላፊነት ተሰጥቶት ኃላፊነቱን አከናወነ። ከዚያም በዳንግላም ሆነ በመላው አገው ምድር የመጀመሪያ የሆነውን የዳንግላ ትምህርት ቤትን እንዲያቋቁም የተሰጠውን ኃላፊነት ተወጣ። ሀዲስ የትምህርት ቤቱ ዳይሬክተርና መምህር ሆኖ አገልግሏል።

በ1928 ዓ.ም ወደ ደብረ ማርቆስ ተዛውሮ በንጉሥ ተክለሃይማኖት ትምህርት ቤት የእንግሊዝኛና የሂሳብ መምህር ሆነ። የወቅቱ የጎጃም ገዥ የነበሩትን የልዑል ራስ እምሩ ኃይለሥላሴ ልጆችንም ያስተምር ነበር። እስከ ፋሺስት ኢጣሊያ ወረራ ጊዜ ድረስም በዚያው በደብረ ማርቆስ ቆየ።

ፋሺስት ኢጣሊያ ኢትዮጵያን በወረረችበት ወቅት ሀዲስ ከመንግሥት ሳይጠብቅ ራሱ ጠመንጃ ገዝቶ፣ የራስ እምሩን ጦር ተቀላቅሎ በአርበኝነት መዋጋት ጀመረ።



ሀዲስ አለማየሁ

የሕዝቡንና የአርበኛውን ስሜት የሚቀሰቅሱ የኪነ ጥበብ ሥራዎችንም እየሠራ አቅርቧል። በ1929 ዓ.ም ጎጀብ ወንዝ አካባቢ በተደረገ ውጊያ ላይ ተማርኮ ፖንዞ እና ሊፓሪ ወደሚባሉና በሳርዲና አካባቢ (ደቡባዊ ኢጣሊያ) ወደሚገኙ የሜዲትራኒያን ደሴቶች ተወስዶ ታሰረ። ከሰባት ዓመታት የእስራት ጊዜ በኋላ አርበኛው ሀዲስ ወደ ኢትዮጵያ ተመለሰ።

ወደ ኢትዮጵያ እንደተመለሰም በማስታወቂያ ሚኒስቴር የፕሬስና ኢንፎርሜሽን ምክትል ዳይሬክተር ሆኖ ተሾመ። ሀዲስ ማስታወቂያ ሚኒስቴር ውስጥ በቆየባቸው ጊዜያት ሚኒስቴሩ በሰው ኃይልና በቁሳቁስ የተደራጀ እንዲሆንና ሥራውን በአግባቡ እንዲያከናውን ስለማድረጉ ቢትወደድ ዘውዴ ገብረሕይወት (የአዲስ አበባ ከተማ ከንቲባ እንዲሁም በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የኢትዮጵያ አምባሳደርና ቋሚ ተወካይ ሆነው ያገለገሉ) ምስክርነታቸውን ሰጥተዋል። ከዚያም ወደ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተዛውሮ የአሜሪካ ጉዳዮች ክፍል ዳይሬክተር ሆነ።

በ1938 ዓ.ም አቶ ሀዲስ አለማየሁ በኢየሩሳሌም የኢትዮጵያ ቆንስላ ተጠሪ ሆነው ተሾሙ። በዚህ ወቅት ነው የትዳር አጋራቸውን ወይዘሪት ክበበፀሐይ በላይን ያገኙት። የዋግሹም ተፈሪ ወሰን የልጅ ልጅ የሆነችው ወይዘሪት ክበበፀሐይ በወቅቱ በወይዘሮ አማረች ወለሉ አሳዳጊነት በኢየሩሳሌም ትኖር ነበር። በ1939 ዓ.ም በአትላንታ የቴሌኮሙኒኬሽን ጉባዔ ላይ ኢትዮጵያን በመወከል ወደ አሜሪካ ተጉዘው ለአምስት ወራት ያህል በአሜሪካ ቆይተዋል። በዚህ ወቅት ኢትዮጵያን በመወከል በሌሎች ጉባዔዎች ላይም ተሳትፈዋል። በመቀጠልም በዋሺንግተን ዲ.ሲ የሚገኘውና በራስ እምሩ ኃይለሥላሴ የሚመራው የኢትዮጵያ ለጋሲዮን ዋና ጸሐፊ ሆኑ። ከዚህ ኃላፊነታቸው ጎን ለጎን መደበኛ ባልሆኑ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጉባዔዎች ላይ ኢትዮጵያን በመወከል አገልግለዋል። በ1941 ዓ.ም በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባዔ የሽግግር ኮሚቴ የኢትዮጵያ ተወካይ ሆኑ። አቶ ሀዲስ በወቅቱ በአሜሪካ በነበራቸው ቆይታ በዋሺንግተን ዩኒቨርሲቲ የዓለም አቀፍ ሕግ ትምህርት ጀምረው የነበረ ቢሆንም ወደ ኢትዮጵያ እንዲመለሱ በመታዘዛቸው የጀመሩትን ትምህርታቸውን ሳያጠናቅቁት ቀርተዋል።

በ1942 ዓ.ም ወደ ውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ተመልሰው የሚኒስቴሩ የፕሬስና ዓለም አቀፍ ጉዳዮች ዳይሬክተር ጀኔራል ሆነው መሥራት ጀመሩ። ከሁለት ዓመታት ቆይታ በኋላ ደግሞ ምክትል የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሆነው ተሾሙ። በዚህ ኃላፊነታቸው ላይ በነበሩበት ወቅት አሜሪካ በኢትዮጵያ የውስጥ ጉዳይ ላይ የነበራትን ጣልቃ ገብነትና ጫና አምርረው ይቃወሙ ነበር። ጆን ስፔንሰር ከተባለው አሜሪካዊ አማካሪ ጋርም ሰፊ የሃሳብ ልዩነት ነበራቸው። ስፔንሰር «Ethipia at Bay - A Personal Account of The Haile-Selassie Years» የሚል ርዕስ በሰጠው መጽሐፉ፣ « ... ራስ እምሩ፣ ሀዲስ ዓለማየሁ፣ ሲራክ ኅሩይ ... ኮሙኒስታዊ እሳቤ አላቸው ...» በማለት ጽፏል። ከዚህ በተጨማሪም ኢትዮጵያ ከአሜሪካ ጋር ያላትን ግንኙነት ከማይደግፉና ከሶቭየት ኅብረት ጋር ግንኙነት እንድትመሰርት ካደረጉ ሰዎች መካከል አንዱ ሀዲስ እንደነበሩ ስፔንሰር ገልጿል። በሀዲስ የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች ላይ ጥናት ያደረጉት ጸጋዬ ኃይሉ ግን፤ ሀዲስ ከምስራቁ ይልቅ የምዕራቡ ዓለም ርዕዮተ ዓለማዊ እሳቤን ይመርጡ እንደነበር ጽፈዋል። ቢትወደድ ዘውዴ ገብረሕይወት እና ብላታ መሐሪ ካሣ በበኩላቸው፤ ሀዲስ ዓለማየሁ ለምስራቁም ሆነ ለምዕራቡ ርዕዮተ ዓለም የተለየ ፍላጎት አልነበራቸውም። የእርሳቸው ዋነኛ ጉዳይ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅምና ሉዓላዊነት ነበር» በማለት መስክረዋል። በእርግጥ ሀዲስ አለማየሁ «ኢትዮጵያ ምን ዓይነት አስተዳደር ያስፈልጋታል?» በሚለው ሥራቸው ላይ « .... ኢትዮጵያ ካፒታሊዝምንም ሆነ ሶሻሊዝምን ከመምረጥ ይልቅ ከሁለቱም ወገኖች ጥሩ የሚባሉትን ሃሳቦች በመውሰድ ከራሷ ታሪክ፣ ባሕልና ማኅበረሰብ ጋር የሚጣጣም አድርጋ መቅረፅ ያስፈልጋታል ...» ብለዋል።

ሀዲስ በዲፕሎማትነት ዘመናቸው ኢትዮጵያን ወክለው ከተሳተፉባቸው አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ጉባዔዎች መካከል የዓለም የምግብና የእርሻ ድርጅት ጉባዔ (እ.ኤ.አ 1948፣ሮም)፣ አራተኛው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባዔ (እ.ኤ.አ 1949፣ኒው ዮርክ)፣ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባዔዎች (እ.ኤ.አ 1952፣ኒው ዮርክ እና 1956፣ፓሪስ) እና የአፍሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሮች ጉባዔ (እ.ኤ.አ 1964፣ሌጎስ) ይጠቀሳሉ።

እ.ኤ.አ በ1956 በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የኢትዮጵያ አምባሳደርና ቋሚ ተወካይ ሆነው በተሾሙበት ጊዜ ዋነኛ ተግባራቸው፤ የኢትዮጵያና የኢጣሊያ ሶማሊላንድ የድንበር ጉዳይ ነበር። ስፔንሰር ሀዲስ በድንበር ላይ የነበራቸውን አቋም ሲገልፅ « ... የኢትዮጵያ ንብረት የሆነችን ቅንጣት ታክል ቁራሽ መሬት የመስጠት ፍላጎትና ዝግጁነት አልነበረውም ...» ብሏል። በዚህም ነው ሀዲስ ስለድንበሩ ጉዳይ የሚደራደረው የኢትዮጵያ ቡድን መሪ ተደርገው የተሾሙት። ምንም እንኳን የድንበር ማካለል ድርድሩ ያለስምምነት ቢጠናቀቅም፤ ሀዲስ የኢትዮጵያን ጥቅም ለማስከበር ብርቱ ጥረት አድርገዋል።

በመንግሥታቱ ድርጅት የነበራቸውን የአራት ዓመታት ከአምስት ወራት ቆይታ ሲያጠናቅቁ የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ ሆነው ተሾሙ። በዚህ ወቅት ነበር ሀዲስ «ልዩ ማስታወሻ» የሚል መልዕክት ለንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ ያቀረቡት። በዚህ መልዕክታቸው በ1953 ዓ.ም የተሞከረው መፈንቅለ መንግሥት መንስኤና ወደፊትም የመንግሥት አሠራር ካልተሻሻለ የከፋ ችግር ሊያጋጥም እንደሚችል በመጥቀስ ኋላ ቀር የሆነው የኢትዮጵያ ማኅበረ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መዋቅር ሊሻሻል እንደሚገባ ገልጸዋል። ይህ መረር ያለ የሀዲስ ምክረ ሃሳብ ሥልጣናቸውንና ክብራቸውን እንደዓይናቸው ብሌን ለሚጠብቁት ለንጉሠ ነገሥቱ ምቾትን አልሰጠም። ንጉሠ ነገሥቱ ሀዲስን ቢሯቸው አስጠርተው «ድፍረት ስለተሞላበት» ደብዳቤያቸው ገሰጿቸው። ሀዲስ ግን በንጉሠ ነገሥቱ ሃሳብ ባለመስማማት በመልዕክታቸው ካሰፈሩት ሃሳብ በተጨማሪ ሌሎችንም ምክረ ሃሳቦችን ለንጉሠ ነገሥቱ ተናገሩ። መልዕክቱ ለንጉሠ ነገሥቱ በደረሳቸው በስምንተኛው ቀን ሀዲስ የትምህርት ሚኒስትር ዴኤታ እንዲሆኑ ተደረገ። ንጉሠ ነገሥቱ ራሳቸው የትምህርት ሚኒስትር ስለነበሩ ሹመቱ ከፍተኛ ትችት የሰነዘሩባቸውን ደፋሩን፣ በግልፅ ተናጋሪውንና ትሁቱን ሀዲስን ከጎናቸው አድርገው ለመቆጣጠር እንደሆነ ግልፅ ነበር።

በአፍሪካ የትምህርት ዘርፍ ላይ ያተኮረ ጉባዔ ሲካሄድ፤ ሀዲስ በኢትዮጵያ ስለነበሩት ትምህርት ቤቶችና ተማሪዎች ቁጥር ያቀረቡት ሪፖርት ንጉሠ ነገሥቱን አናደዳቸው። ይህም የንጉሠ ነገሥቱንና የሀዲስን ቅራኔ እያሰፋው ሄደ። ከዚህ በተጨማሪም ሀዲስ ከሌሎች ባለሙያዎች ጋር በመተባበር ባዘጋጁት የትምህርት ዘርፍ እቅድ ላይ፣ ለዘርፉ ከሚመደበው በጀት መካከል 25 በመቶ ያህሉ ብቻ ለአስተዳደራዊ ጉዳዮች እንዲሆንና ቀደም ሲል ለአስተዳደራዊ ጉዳዮች ሲመደብ የቆየው 75 በመቶ የዘርፉ በጀት ትምህርት ቤቶችን ጨምሮ ለትምህርት ግብዓቶች ማሟያ እንዲውልና እቅዶችን ከማዘጋጀትና አፈጻፀሞችን ከመከታተል በስተቀር ያሉት ሥራዎች በዘርፉ ባለሙያዎች ብቻ እንዲከወኑ ያቀረቡት ሃሳብ ተቀባይነት ሳያገኝ ቀረ። በዚህ ጊዜ ሀዲስ መንግሥት የትምህርት ዘርፉን ለመለወጥ ፍላጎት እንደሌለው በማመናቸው ከሥልጣን መልቀቂያ አቀረቡ። በመቀጠልም ለአምስት ዓመታት ያህል በእንግሊዝና እና በኔዘርላንድስ የኢትዮጵያ አምባሳደር ሆነው አገለገሉ። ሀዲስ እንግሊዝ በነበሩበት ወቅት ባለቤታቸው ወይዘሮ ክበበፀሐይ በላይ አረፉ። በልጅ ያልታጀበው ጋብቻ በዚሁ ተቋጨ፤ ሀዲስም በድጋሚ ወደ ትዳር አልተመለሱም። አዲስ አበባ ቀጨኔ አካባቢ የሚገኘውን ቤታቸውንም ለሕፃናት ማሳደጊያ እንዲሆን ለከተማው አስረከቡ።

ፀሐፌትዕዛዝ አክሊሉ ሀብተወልድ ጠቅላይ ሚኒስትር ሆነው ሲሾሙ፤ ሀዲስ ከለንደን ተመልሰው የእቅድና ልማት ሚኒስትርነቱን ያዙ። ሀዲስ፤ የተማሩ ወጣት ኢትዮጵያውያንን በማሰባሰብ ሚኒስቴሩ በሰው ኃይል የተደራጀ እንዲሆን አደረጉት። ሦስተኛው የአምስት ዓመት የልማት እቅድ (Third Five Year Development Plan) የተዘጋጀውም በዚህ ወቅት ነበር። ይሁን እንጂ ለእቅዱ ማስፈጸሚያ የተመደበው በጀት ሲቀነስ ሀዲስ ባለመስማማታቸው በድጋሚ ከኃላፊነታቸው ለቀቁ። ከዚያም እስከ የሕግ መወሰኛ ምክር ቤት አባል ሆነው እስከ አብዮቱ ፍንዳታ ድረስ ቆዩ።

ደርግ ተመስርቶ ልጅ እንዳልካቸውና ካቢኔያቸው ሥልጣን እንዲለቁ ጥያቄ ሲያቀርብ ጠቅላይ ሚኒስትር እንዲሆኑ በግንባር ቀደምትነት ያጫቸው ሰው ሀዲስ አለማየሁ ነበሩ። በሌተናንት ጀኔራል አማን ሚካኤል አንዶም በኩል ለጠቅላይ ሚኒስትርነት መታጨታቸው የተነገራቸው ሀዲስ ግን፤ የደርግን ዝርዝር ዓላማና ፕሮግራም የሚያስረዳቸው ሰው ሳያገኙ በመቅረታቸው በዕጩነታቸው ሳይስማሙ ቀሩ። ደርግ ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴን ከዙፋን አውርዶ ራሱን «ጊዜያዊ ወታደራዊ መንግሥት» ብሎ ሰይሞ መንግሥታዊ ሥልጣን ከጨበጠ ከዓመት በኋላ ባቋቋመውና ከየአካባቢው የተወከሉ እውቀትና ልምድ ያላቸው ግለሰቦች በተካተቱበት የመማክርት ሸንጎ ውስጥ ጡረታ እስከወጡበት ጊዜ ድረስ ለሁለት ዓመታት ያህል አገልግለዋል።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን (UN Economic Commission for Africa) አዲስ አበባ ላይ እንዲቋቋም የተደረገው በሀዲስ አለማየሁ ብርቱ ጥረት ነው። ሀዲስ በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የኢትዮጵያ አምባሳደርና ቋሚ ተወካይ በነበሩበት ወቅት ብዙ የአፍሪካ ሀገራት በቅኝ ግዛት ቀንበር ስር ስለነበሩና ቅኝ ገዢዎች ቅኝ የሚገዟቸውን እንዲለቁ ሲጠየቁ ከሚያቀርቧቸው ምክንያቶች መካከል አንዱ ሀገራት «አብዛኞቹ የአፍሪካ አገሮች ነጻ ቢወጡ በኢኮኖሚ ራሳቸውን አይችሉም» የሚል ነበር። ሀዲስም ምክንያት ነው ተብሎ የቀረበው ነገር ቅኝ ገዢዎቹ ጭቆናቸውን ለማራዘም የሚጠቀሙበት ዘዴ መሆኑ ስለገባቸውና አፍሪካን በዘላቂነት ከቅኝ ግዛት ማላቀቅ የሚቻለው የአፍሪካውያንን ትብብር በማጠናከርና የአሕጉሪቷን የኢኮኖሚያዊ ችግሮች መፍታት ሲቻል መሆኑን በማጤን አንድ አፍሪካዊ ተቋም እንደሚያስፈልግ አምነውበት ሃሳባቸውን ለንጉሠ ነገሥት ቀዳማዊ አፄ ኃይለሥላሴ አቅርበው የአፍሪካ የኢኮኖሚክ ኮሚሽን አዲስ አበባ ላይ ሊቋቋም ቻለ።

ሀዲስ አለማየሁ በብዙ ኢትዮጵያውያን ዘንድ የሚታወቁት ዘመን ተሻጋሪና አስደናቂ በሆኑ የሥነ ጽሑፍ ሥራዎቻቸው ነው። ሀዲስ «ፍቅር እስከ መቃብር»፣ «ወንጀለኛው ዳኛ»፣ «የልምዣት»፣ «ትዝታ»፣ «ተረት ተረት የመሰረት፣ «ኢትዮጵያ ምን ዓይነት አስተዳደር ያስፈልጋታል?»፣ «ሐበሻና የወደኋላ ጋብቻ»፣ እና «የትምህርትና የተማሪ ቤት ትርጉም» የተሰኙ ልብ ወለዳዊና ኢ-ልብ ወለዳዊ የድርሰትና የተውኔት ሥራዎችን አበርክተዋል። በተለይ «ፍቅር እስከ መቃብር» የተሰኘው ሥራቸው በኢትዮጵያ የአማርኛ ሥነ ጽሑፍ ታሪክ ውስጥ ከታዩ ሥራዎች መካከል ከግንባር ቀደምቶቹ ተርታ የሚሰለፍ ሆኖ ዘልቋል። ለሥነ ጽሑፍ ሥራዎቻቸውም የቀዳማዊ ኃይለሥላሴ የሥነ ጽሑፍ ሽልማትን አሸንፈዋል። አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ደግሞ የክብር ዶክትሬት ዲግሪ ሰጥቷቸዋል። ደብረ ማርቆስ ዩኒቨርሲቲ ያሰራላቸው ከነሀስ የተቀረፀ ሐውልት በ2009 ዓ.ም በደብረ ማርቆስ ከተማ ቆሞላቸዋል። የኢትዮጵያ ደራሲያን ማኅበርም በ2002 ዓ.ም ለክብር ዶክተር ሀዲስ አለማየሁ ያዘጋጀው የፖስታ ቴምብር በኢትዮጵያ የፖስታ ድርጅት ታትሞ ተሠራጭቷል።

በኢትዮጵያ የፖለቲካና የሥነ-ጽሑፍ ዘርፎች ላይ ገናና ስም የነበራቸው ደራሲ፣ መምህር፣ ፖለቲከኛ፣ አርበኛ፣ ባለቅኔ፣ ... የክብር ዶክተር ሀዲስ አለማየሁ ኅዳር 26 ቀን 1996 ዓ.ም በ94 ዓመታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ተለይተዋል። ሥርዓተ ቀብራቸውም በአዲስ አበባ፣ በመንበረ ጸባዖት ቅድስት ሥላሴ ቤተክርስቲያን ተፈፅሟል።

ስፖርት እና መዝናኛ

# የዝነኞች ገጽ

# ቄሳር የቀበረው አልማዝ

**ሙሉጌታ ብርሃኑ**

ዝነኞቹን ፍለጋ የዘመን ቁልቁለቱን ይዘን በመውረድ በሁለት ክፍለ ዘመናት መካከል ኖረው፣ ሠርተው፣ ጥበብን ከጥበብ ስጋና ደም ፈጥረው እስትንፋስ የሰጡ አንድን ሰው እናገኛለን። እኚህ ሰውም አልማዝ፣ ሥራዎቻቸውም እንቁ ነበሩ። ዳሩ ግን የፋሽስት ጥሩር ከደረቱ የታጠቀው የቄሳር መንግሥት በክፉ ዓይኑ አይቷቸው ይሁን በእንቁ ተመኝቷቸው...አልማዙን ሰው ከእምጥ ስምጥ ሰወራቸው።

ከእናት ሀገራቸው ዘርፎ፣ በገዛ አፈሯ ውስጥ ቀበራቸው። አልማዙ ሰው በአንድ ወቅት የነጋዴው ሁሉ ራስ የነበሩት ነጋድራስ አፈወርቅ ገ/እየሱስ ናቸው። ነጋድራስነቱን ከአጼው ያገኙት የሥልጣን መንገድ ቢሆንም ከዚያ ይልቅ ግን የነብስ ጥሪያቸውን መንገድ ይዘው ለጥበብ ብዙ አትርፈዋል። መቼም "ጦቢያ"ን ያህሉን መጽሐፍ የማያውቅ የለም። በሀገራችን የሥነ ጽሁፍ ታሪክ ውስጥ ዝነኛው መጽሐፍ ነው። መጽሐፍ ብቻም ሳይሆን የመጀመሪያው የሀገራችን ልቦለድም ጭምር ነው። ታዲያ ይህን የጻፉትም እኚሁ ሰው ናቸው።

ግጥም እንደመግጠምም ብለው ብዙ ስንኞችን ቋጥረዋል። በስዕል ደረጃ ስማቸው ከፍ ተደርጎ ባይወሳም ጎበዝ ሰዓሊ ነበሩ። የእኚህ ሰው ታሪክ በመሃል አገም ጠገም በዝቶበት እክል ገጠመውና እንደ ሥራቸው እንዳይነገርላቸው በመሃል ቤት ላይ ቆመዋል። ይሁንና የጋመ ፍም አመድ ቢደፋበት አይታይ ይሆናል እንጂ ማቃጠሉ አይቀርም። ሥራዎቻቸውን ጥበብ አትረሳውም። ታሪክም አይፍቀውም።

ነጋድራስ አፈወርቅ ገ/እየሱስ ሐምሌ 10 ቀን 1861 ዓ.ም በደቡባዊው የጣና ሀይቅ ዙሪያ በምትገኘው በዘጌ ስለመወለዳቸው ይነገራል። ልጅ ሆነው እንደማንኛውም የዘጌ ልጅ በመንደሯ ተሯሩጠው፣ ምናልባትም ደግሞ የከብቶችን ጭራ ተከትለው፣ ከግጦሹም አሰማርተውና ከጉድባው ላይ ዋሽንቱን ነፍተው ይሆናል። የታሪክ ማህደራቸው ግን፤ በዚያው በሚገኘው ኪዳነ ምህረት ገዳም ውስጥ በአያታቸው መምህር ድንቄ የአብነት ትምህርት ስለመቅሰማቸው ይናገራል።

ሌላው ከውልደት ሰሞን ታሪካቸው መካከል ከሚነገርላቸው አንዱ የእቴጌ ጣይቱ ብጡል የስጋ ዘመድ ስለመሆናቸው ነው። ለዚህም ይሆናል አፈወርቅ የትውልድ ቀያቸውን ለቀው አዲስ አበባ፣ ከአዲስ አበባም ወደ እንጦጦው ቤተ መንግሥት ቅጥር ጊቢ ለመግባት እምብዛም ዕድሜ አልፈጀባቸውም። በመጀመሪያው አመጣጣቸው በባለሟልነት ሲያገለግሉ ጥቂት ቆዩ። በስዕል ጎበዝ ከመሆናቸውም ውስጣቸው ዕውቀትና የልጅ አዋቂነት እንዳለ ግን ለአጼ ምኒልክ ቁልጭ ብሎ ይታያቸው ነበር።

ከባለሟልነት ወደ ዙፋን አገልጋይነት፣ ከጉልበታቸው ዕውቀታቸው ይበልጥ እንደሚያስፈልጋቸው የተረዱት አጼ ምኒልክ አፈወርቅ ቢማርና ያለውን ቢያዳብር የተሻለ መሆኑን አመኑበት። የ20 ዓመት አፍላ ወጣት ሳለም ለትምህርት ወደ ባህር ማዶ ሊሰዱት አሰቡ። እናም ልጅ ቅጣውንና ጉግሳ ዳርጌን አክለው በ1880ዓ.ም ወደ ሲዊዘርላንድ ላኳቸው። አጼው በብልህነታቸው ባህላቸውን ሳያስነኩ በአውሮፓ የሥልጣኔ ቀንበጥ የተነደፉ ነበሩ። ሲወዱና ሲደፍሩ ልክ አልነበራቸውም።

ሁሉንም ማየት፣ መልካም መልካሙንም ለሀገራቸው የማድረግ ፍላጎታቸው ከፍተኛ ነበርና ይህን ለማምጣት አንድም ወጣቶችን ለትምህርት በመላክ ነበር። በዚህ እሳቤ ከተላኩት አንዱም አፈወርቅ ነበር። የላኳቸው ሦስቱ ወጣቶች ሲዊዘርላንድ ደርሰው ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ እንደሆኑ ሲያስቡ ለነበሩት ለንጉሡ የኋላ ኋላ አንድ ነገር ደረሳቸው። አፈወርቅ ሲዊዘርላንድን ከረገጠ በኋላ ምንም ባልታወቀ ምክንያት ሹልክ ብሎ ኢጣሊያ መግባቱን ነበር። እንግዲህ "መንገዱን ጨርቅ ያድርግልህ" ይሉት ይሆናል እንጂ ሌላ ምንስ ሊሉት ይችላሉ።

አፈወርቅ ወደ ኢጣሊያ ካቀኑ በኋላ በቱሪን "ኢንተርናሲዮናል ደ.ቤሊ. አርቲ" በተባለ ኮሌጅ ውስጥ ላቅ ያለ የሥነ ጽሁፍ ትምህርት መከታተል ጀመሩ። ምናልባትም ከሲዊዘርላንድ የመኮብለላቸው ምክንያት ሊሆን የሚችለው ይሄው ነው። የሚፈልጉትን ሳይሆን የሚፈለግባቸውን እንዲማሩ የተፈረደባቸው ስለመሰላቸው ውስጣቸው የሚላቸውን ተከትለው ራሳቸውን ነጻ ለማውጣት ይሆናል ወደ ኢጣሊያ ዞረው ይህን መምረጣቸው።

ይሁንና ከዓድዋው የፋሽስት ጦርነት ቀድመው ኢትዮጵያ የገቡት ነጋድራስ አፈወርቅ ገ/እየሱስ ነበሩ። ትዕዛዝ ጥሰው ከተላኩበት ወደ ሌላ የኮበለሉ ቢሆንም ተመልሰው ሲመጡ ግን የቤተ መንግሥቱ በር አልተዘጋባቸውም። ለዚህ ደግሞ እንደምናልባት ልናነሳት ከወደድን ኢጣሊያ ሳሉ የፈጸሟት አንዲት ግብር ነበረቻቸው። በዚያው ሳሉ ራስ መኮንን ከኢትዮጵያ ተነስተው በሥራ ጉብኝት ኢጣሊያ ገብተው ነበርና አፈወርቅ ደግሞ በአስተርጓሚ፤ ቱርጅማንነት ረድተዋቸዋል።

ራስ መኮንንም ሲመለሱ ይህንኑ ለንጉሡ ነግረው አሰርየውላቸው ይሆናል። አፈወርቅም አዲስ አበባ ገብተው የሀገራቸውን አፈር እንደረገጡ ዳግም ወደዙፋኑ ጠጋ ማለታቸው አልቀረም። ብዙ አገልግሎትም ሲሰጡ ነበር። በእንጦጦ ራጉኤልና እንጦጦ ማርያም አቢያተ ክርስቲያናት ውስጥ ቆንጆ ቆንጆ የግርግዳ ላይ ስዕሎችን የሳሉትም በዚህ ወቅት ነው። ሃሳቡን ያመጡት እቴጌ ጣይቱ ነበሩ። ቢሆንም ግን የዙፋኑ ንግሥትና ዘመዳቸው ከሆኑት እቴጌ ጣይቱ ጋር ሊስማሙ አልቻሉም። ተቀያየሙናም አፈወርቅ መልሰው ለስደት ሻንጣቸውን ሸከፉ።

በ1888ዓ.ም ወደመጡበት ኢጣሊያ ተመልሰው ሄዱ። የተማረችባቸው ኢጣሊያም እጇን ዘርግታ ተቀበለቻቸው። እሳቸውም ለእነርሱ የነበራቸው ፍቅር የዋዛ አልነበረም። ናፖሊ ከተማ ውስጥ በሚገኘው የምሥራቅ ጥናት ተቋም ውስጥ የአማርኛ ቋንቋን ማስተማር ጀመሩ። በኋላም የፕሮፌሰርነትን ማዕረግም ሰጥቷቸዋል።

በሀገራችን የመጀመሪያው ልቦለድ ለመባል የበቃው "ጦቢያ"ን የጻፏት እዚያ ሳሉ ነበር። በ1908ዓ.ም በሮም ታትማ ለመነበብ በቃች። 90 ገጾች ብቻ የያዘች አነስተኛ መጽሐፍ ብትሆንም ታሪክና ክብረ ወሰኗ ግን ትልቅ ነበር። የኢትዮጵያ የዘመናዊ ሥነ ጽሁፍ አብዮት ተኳሽና መሠረት ሆና እንድትቆጠር፣ አፈወርቅም ሌላ ከፍታ ላይ እንዲቀመጡ ሆናለች። በዚህች ልቦለድ የሠበሩት ክብረ ወሰን ከኢትዮጵያ አልፎ በአፍሪካ ታሪክ በሀገርኛ ቋንቋ መጽሐፍ የጻፈ የመጀመሪያው ጥቁር አፍሪካዊ ለመባልም ችለዋል።

ሁለት ጊዜ ከሀገር የወጡት ነጋድራስ አፈወርቅ ሁለት ጊዜ ወደ ሀገር ተመልሰዋል። ከመጀመሪያው የሁለተኛው አካሄዳቸው ላይመለሱ ቢመስልም 1922ዓ.ም እንደገና ወደ ሀገር ተመለሱ። ከዚህ በኋላም በርከት ያሉ የመጽሐፍት ሥራዎችን ለማበርከት ችለዋል። በአማርኛና ግዕዝን ጨምሮ በኢጣሊያንኛና ፈረንሳይኛ ቋንቋዎች የመማሪያ መጽሀፍት አዘጋጅተዋል። "ጦቢያ" በክብሩ እንዳለም፤ ዕውቅ ከሆኑት የነጋድራስ ሥራዎች መካከል "የኢትዮጵያ መንግሥት አልጋ ወራሽ"፣ "ዳግማዊ ምኒልክ ንጉሠ ነገሥት ዘ ኢትዮጵያ"፣ "ሚናስ"፣ "ዘንዶ ሲነግስ"፣ "ክሊዎፓትራና ማርካንትዋን" ተጠቃሾች ናቸው። ጽፈው ለህትመቱ ያላበቋቸው ሌሎች የልቦለድ ሥራዎችም ነበሯቸው።

የ20ኛው ክፍለ ዘመን አጀማመር ለአፈወርቅ መልካምና ከእናት ሀገራቸው እቅፍ ውስጥ የሞቃቸው ይመስላል። በመጽሐፍት ሥራዎቻቸው ስመ ጥር ሆነዋል። በአጼ ምኒልክ መጨረሻና በጃንሆይ መጀመሪያ ተቀባይነትም አግኝተዋል። ከሠሩትና ካላቸው አዋቂነት የተነሳ ከዙፋኑ በታች ባሉ የሥልጣን ወንበሮችን ለማግኘትም ችለዋል። በድሬዳዋ ባለው ጉምሩክ ላይ ተሹመው "ነጋድራስ" የሚለውን ማዕረግ አገኙ።

ቀጥሎም በጊዜው በነበረው አሸማጋይ ፍርድ ቤት ፕሬዚደንት ሆነው ተቀመጡ። በሌላ ጊዜም አብዝተው ወደሚወዱት የኢጣሊያ ቀዬ መግቢያ የሥልጣን በትር ተረከቡ። የኢትዮጵያ እንደራሴ (አምባሳደር) ሆነው በሮም ተሰየሙ።

ታላቁ ሰው በቄሳር...አንዳንድ ጊዜ የማንጠብቀውን ሰው ከማንጠብቀው ሥፍራ ላይ እናገኘው ይሆናል።



ነጋድራስ አፈወርቅ ገ/እየሱስ፣

የነጋድራስ በቄሳር ቤት ውስጥ የመገኘት ነገር ለብዙሃኑ ውል አልባ ጉዳይ ነው። የሆነውም እንዲህ ነበር... ጊዜው ከ19ኛው ወደ 20ኛው ክፍለ ዘመን ሽግግር ተደርጎበታል። ኢትዮጵያ የመጀመሪያውን የፋሽስት ወረራ ዓድዋ ላይ ድል መታ ሀገር ሰላም ብላ ከተቀመጠች ድፍን ሦስት አሥርት ዓመታት አልፈዋል። ሶላቶው ግን አላርፍ ብሎ እልህ ትንፋሽ ስላሳጣው ዳግም ለወረራ በመሰናዳት ላይ ነበር።

አንድ ጊዜ እዚህ ሌላ ጊዜ ደግሞ እዚያ በማለት ውሉ የጠፋባቸው ነጋድራስ አፈወርቅ የት መሆን እንዳለባቸው ጭንቅ ጥብብ ያላቸው ይመስላል። ይሁንና ፋሽስቱ ኢጣሊያ የጦር ግሳንግሱን ሰብስቦ ወረራውን ተያያዘው። ከዚያ ቀደም የሰውየው አብዝቶ ከኢጣሊያውያኑ ጋር ሽር ብትን ማለት አዝማሚያው ያላማራቸው ወትሮም በሀሜት ጎሰም ሲያደርጓቸው ነበር። ጦርነቱ ሲጀምር ደግሞ ሀሜቱ እውነት ስለመሆኑ በብዙዎች ታመነ። በኋላም ቢሆን ለእውነታው ማስረገጫነት ሲነሳ የነበረው የቄሳር መንግሥት መልዕክተኛ ጋዜጣ ነበር።

የዚህ ጋዜጣ አዘጋጅ በመሆን መሥራት በመጀመጀመራቸው ነው። ይባስ ደግሞ ከዚያኛው ወገን የአፈ-ቄሳርነትን ማዕረግ ደረቡላቸው። እንግዲህ በዚህ መጀቦናቸው ቢሞቃቸውና ከቄሳር ለቄሳር የሚሠሩ "አፍቃሪ ቄሳር" ቢሆኑ ነው ሲል የሀገሬው ሰው አመነ። ከአህያ ጋር የዋለች ጊደር ብትማር ፈስ ነው። ከባንዳነት ሌላ ምን ሊኖራቸውና፤ ሲል ከሶላቶው ጋር ሶልተው በዚያ ወገን ስለመቆማቸው ዙፋኑም እርግጠኛ ሆነ።

በኢጣሊያና በኢትዮጵያ፣ በፋሽስትና በአርበኛው መካከል ጦርነቱ ተጧጡፎ እየከረረ ሄደ። ንጉሡም መፍትሄ ፍለጋ፣ በአውሮፓ 'ሊግ ኦፍ ኔሽን' አቤት ለማለት ወደ እንግሊዟ የኤልሳቤት ዙፋን ተጠጉ።

ዳሩ የመጣ ሁሉ ይሄዳል። የሄደም ይመለሳል። በመምጣትና መሄድ ተናውጣ ሥፍራዋን የማትለቅ ሀገር ብቻ ናት። ንጉሡም ከእንግሊዝ መጡ። ፋሽስቱም ጨርቅና ማቁን ሰብስቦ ወጣ። የዘውዱም ዙፋን ዳግም ጸና። ነጋድራስ ግን "የሀገሬ ጅብ ይብላኝ። አፈሯም በላዬ ይማስብኝ" ብለው ነው መሰል፤ መልቴ ከተባሉበት ከሶላቶው ጋር አብረው አልወጡም ነበር። ላይ ታች ውጣውረዱ ሁሉ አክትሞ በ1933 ዓ.ም ሀገር ነጻነቷን እንዳስመለሰች አይቀሬው የክስ ጎራዴ ተመዘዘባቸው።

"በጦርነቱ ወቅት በሀገር ክህደት ለቄሳር መንግሥት ወግነው ቆመዋልና የሞት ፍርድ ይፈረድባቸው!" ተባለ። ይህን ጊዜ ነጋድራስ ሲሰሙ፤ ምን ግጥም ገጥመው፣ እንዴት ሲሉ ጽፈውና ምን መልክ ያለውን ስዕል ስለው እንደሆን ግን እንጃ...ብቻ በባንዳነት ከመጠርጠር አልፈው፣ በፍርድ የሞት ሸንጎ ላይ ሊቆሙ ሆነ።

አሁን ሁሉም የሚጠብቀው የጃንሆይን ትዕዛዝና ፍርድ ነው። ፍርዱን አጽንቶ የመግደል፣ ሀጢያቱንም ሽሮ የማንጻት ሥልጣን የንጉሡ ነው። ግን ሀገር የከዳን ሰው ኩነኔ በምን ሊያስተሰርዩለት ይቻል ይሆን? ጃንሆይስ የቄሳርን ወይንስ የፒላጦስን ፍርድ ሊፈርዱ?

ጃንሆይ በጉዳዩ ብዙ ያሰላሰሉበት፣ አዋቂዎቻቸውንም የመከሩበት ሳይሆን አይቀርም። ግልፍ ብሎባቸው "ስቀሉት! ይህን ባንዳ" አላሉም። እልካቸውን መወጣጫ አላደረጓቸውም። ይልቁንስ ለሞት የተመዘዘውን ካራ ወደሰገባው አስመለሱት። ነጋድራስ እርጅናውም ስለተጫጫናቸው የተፈጥሮ ሞት በራሱ እየገሰገሰ ከደጃቸው መድረሱንም ጃንሆይ ተመልክተው ነበር።

ለሞት የተሰናዳውን የነጋድራስን የአንገት ገመድ ፈተው ባይሆን በሚል ፍርዱን በሌላ ለወጡት። ነጋድራስ አፈወርቅ ገ/ኢየሱስ በሀገር ላይ ክደት መፈጸማቸውን ጃንሆይም አምነው ነበርና ከሞት ፍርድ ወደ እድሜ ልክ እስራት ቀየሩላቸው። በደል ለፈጸሙባት ሀገር ሠርተው ውለታን ውለውላት ነበርና ጃንሆይም ይህንን አልዘነጉትም። የፍርዱ ለውጥ አንድም በዚሁ ነው። እናም ጉዟቸው ከመቃብር ወደ ዘብጥያ ሆነ። ከፍርድ መልስ የነበረው የነጋድራስ ሕይወት በጅማ ጅሬን እስር ቤት ውስጥ ነበር። ከዚያን በኋላ እርጅናው ላይ የጤና መጓደሎች እየታከሉባቸው በእስር ከስድስት ዓመታት በላይ ለማስቆጠር አልቻሉም።

የተፈረደባቸው የእድሜ ልክ እስራት ቢሆንም እድሜ ልካቸው ግን 6 ዓመት ብቻ ነበረች። የ79 ዓመቱ ነጋድራስ መስከረም 15 ቀን 1939 ዓ.ም ክልትው አሉ። የሰው ልጅ የፈረደባቸው እድሜ ልክ በጣት የምትቆጠረዋ 6 ብቻ ናት። እንግዲህ የምድሩ በሰማይ ቀጥሎ ይሁን ለበደሉ ተከሰው የሚያውቅ አንድዬ ብቻ ነው።

ከብዙ ሀጢያት መካከል ያለች አንዲት ጽድቅ መድሃኒት ናት። ባትሽር ባትፈውስ እንኳን እድሜን ታረዝምና ትቀጥላለች። ቢያንስ የበደልነውን የምንክስበትን የጊዜ ዕድል ትሰጠናለች። የበደሉንን ይቅር እንደማለትስ ምን ታላቅነት ይኖራል? እንኳንስ ስቶ የወደቀውን የሀገር ባለውለታን ቀርቶ ሶላቶውንስ ፋሽስት ይቅር ብለን የለም እንዴ? ከሰይጣኑ ጋር ታርቀን ሰይጣን ያሳተውን ብንኮንን አሁን ኩነኔው በኛው ላይ ነው።

ጡት ነካሽነቱን ሳናውቅለት ከነበሽታው በላያችን ላይ የሾምነው ብዙ ነውና ደርሰን አሁን ድረስ ግንፍል ብንል ራስ ማቆሸሽ ነው። ለነጋድራስም ጽድቁ ቆርቶባቸው እንኳን በሥራዎቻቸው ስለሥራዎቻቸው ስንል ልንታረቃቸው ግድ ነው። ታዲያ በአንድ ወቅት ይህንኑ በማሰብ በቴምብሩ ላይ ፎቶዋቸውን ያወጣው የኢትዮጵያ ደራሲያን ማህበር አይገጥሙ ትግል ገጥሞት ነበር። እንዴትስ ነው የአንድን ባንዳ ሰውዬ ምስል በዚህ መልክ መጠቀሙ...ሲል የደነፋው ቀላል አልነበረም።

ጣት ታመመ ተብሎ ተቆርጦ እንዴትስ ይጣላል? ለፈጸሙት ክህደት "ደግ አደረጉ!" ብለን የጀብዱ ሜዳይ ባናጠልቅላቸውም ሥራቸውን ለመካድ ግን አንችልም። በበደላቸው ከመቀጣታቸውም ሌላ አንድ ነገር እንዳስብ አደረገኝ...በጊዜው ፋሽስቱ ጓዙን ጠቅልሎ ሲወጣ ነጋድራስ በሀገር ላይ የእናታቸውን ጡት ስለመንከሳቸው በትክክል ያውቁታል፤ አሊያም ሰምተውታል። በቀጣይ ታላቁ የፍርድ ሸንጎ ላይ ሊቆሙ እንደሚችሉ መቼስ እንደሳቸው የሚያውቀውም አልነበረም።

ጌታዋን የተማመነች በግ ጅራቷን እውጭ ስታሳድር ኋላ ጌታዋ እንደሚያድናት ተማምና ነውና ስለምንስ ጌታዬ ብለው ያገለገሉትን ፋሽስት ተከትለው አልሄዱም? ቀጥሎ የሚከተላቸውን አላጡትም ካልን ሊሆን የሚችለው ጸጸት ነው። የበደልኳትን ሀገር ሸሽቼ ዳግም ከምከዳት ራሷ ትቅበረኝ ብለው ነው። እንጂማ ሳይቀድሙኝ ልቅደም ቢሉ ቤተኛ በሆኑባት ኢጣሊያ መሸሎኪያውን አያጡትም ነበር።

በደላቸውን በይቅርታ ልንሰርይላቸው የሚገባው አንድም በዚህ ተግባራቸው ነው። ሀጢያቱን አውቆ ራሱን ለቅጣት የሚሰጥ የድንጋይ ሳይሆን የስጋ ልብ ነው። ነጋድራስ ለሀገራቸው ባበረከቷት የበኩር ልቦለድ፤ በ"ጦቢያ" ገና በመጀመሪያው ገጽ ላይ ለራሳቸው ትንቢት ይሁን ይህን ጽፈው እናገኛለን "ይቅርታ ጠያቂ ያከበረ፣ ይቅርታ አድራጊውም የተከበረ ነው!" ይላል። በእርግጥ ሁሉም የተከበረ ነው። አልማዝን አቆሸሸው ከአፈር ቢቀብሩትም ያው አልማዝ ነው።

# ዓለም አቀፍ



## ሰሜን ኮሪያ ከሩሲያ ጋር ወግና ለመዋጋት ወታደሮቿን መላኳ ተጠቆመ

ሰሜን ኮሪያ በዩክሬን ከሩሲያ ጋር ወግና ለመፋለም ወታደሮቿን መላክ መጀመሯን የደቡብ ኮሪያ የስለላ ድርጅት አስታወቀ። ይህንን የሰሜን ኮሪያ ርምጃ "ከፍተኛ የደህንነት ስጋት" ስትል ደቡብ ኮሪያ ፈርጃዋለች። ይህ የተሰማው የዩክሬኑ ፕሬዚዳንት ቮሎድሚር ዘለንስኪ 10 ሺህ የሰሜን ኮሪያ ወታደሮች ጦርነቱን ሊቀላቀሉ እንደሚችሉ የደህንነት መረጃዎች ተገኝቷል ካሉ ከአንድ ቀን በኋላ ነው።

የደቡብ ኮሪያው ፕሬዚዳንት ዩን ሱክ ዮል አርብ፣ ጥቅምት 8 ቀን 2017 ዓ.ም በጠሩት የጸጥታ ስብሰባ ዓለም አቀፉ ማህበረሰብ "በሁሉም መንገዶች" ምላሽ መስጠት አለበት ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል። እንደ የስለላ ድርጅቱ ከሆነ እስካሁን አንድ ሺህ 500 የሰሜን ኮሪያ ወታደሮች ወደ ሩሲያ ገብተዋል። አጠቃላይ ለሩሲያ ወግነው የሚዋጉ ወታደሮች ቁጥር ወደ 12 ሺህ ሊጠጋ እንደሚችል የደቡብ ኮሪያ ሚዲያዎች ስማቸው ያልተጠቀሱ ምንጮችን ዋቢ አድርገው ዘግበዋል።

በዩክሬን ፖልታቫ ግዛት ውስጥ ከሚሳኤል ቁርጥራጭ በተገኘ መረጃ ሰሜን ኮሪያ ለሩሲያ የጦር መሣሪያ ታቀርባለች የሚሉ ማስረጃዎች እየጨመሩ መጥተዋል። ሩሲያ እና ሰሜን ኮሪያ በቅርብ ወራት ውስጥ ትብብራቸውን እያሳደጉ መጥተዋል። ለዚህም ማሳያዎች አንዱ የሰሜን ኮሪያው መሪ ኪም ጆንግ ኡን በፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን ልደት ዕለት ደውለውላቸው "የቅርብ ጓዴ" ሲሉ መጥራታቸው ተዘግቧል።

የደቡብ ኮሪያ የብሔራዊ መረጃ አገልግሎት ክስ የመጣው የዩክሬን ወታደራዊ መረጃ ምንጮች የሩሲያ መከላከያ የሰሜን ኮሪያ ጦር ክፍል እየመሠረተ መሆኑን ከገለጹ ከቀናት በኋላ ነው። የዩክሬን የስለላ ድርጅት ኃላፊ ኪሪሎ ቡዳኖቭ በዩክሬን ለመዋጋት ወደ 11 ሺህ የሚጠጉ የሰሜን ኮሪያ እግረኛ ወታደሮች በምስራቅ ሩሲያ እየሠለጠኑ እንዳሉ በዚህ ሳምንት ተናግረዋል ሲል የዘገበው ቢቢሲ ነው።

## ትራምፕ ለሩሲያ እና ዩክሬን ጦርነት ፕሬዚዳንት ዘለንስኪን ተጠያቂ አደረጉ



ትራምፕ ለሩሲያ እና ዩክሬን ጦርነት ፕሬዚዳንት ዘለንስኪን ተጠያቂ አደረጉ። የቀድሞው የአሜሪካ ፕሬዚዳንት እና የ2024ቱ ምርጫ የሪፐብሊካን እጩ ዶናልድ ትራምፕ ለሩሲያ ዩክሬን ጦርነት መጀመር ፕሬዚዳንት ቮለደሚር ዘለንስኪ ተጠያቂ እንደሆኑ ተናገሩ፡፡

በምርጫ ቅስቀሳ መድረኮች እና ቃለ መጠይቆች ፕሬዚዳንቱ ላይ ተደጋጋሚ ትችቶችን የሚሰነዝሩት ትራምፕ "የምድራችን ትልቁ የሽያጭ ሠራተኛ" ሲሉ ዘለንስኪን ወርፈው ነበር፡፡ ዶናልድ ትራምፕ ይህን ያሉት ጦርነቱ ከተቀሰቀሰ በኋላ አሜሪካ እና ምዕራባውያንን በማሳመን ዘለንስኪ በቢሊዮን ዶላር የሚቆጠር ድጋፍ ማግኘታቸውን ባነሱበት ንግግር ነው፡፡

ከዚህ ቀደም በዘለንስኪ ላይ ከተሰነዘሩት ትችቶች ጠንካራ እንደሆነ በተወራለት ንግግር "ምንም እንኳን ጦርነቱ ሩሲያ ዩክሬንን መውረሯን ተከትሎ ቢጀመርም ዘለንስኪ ጦርነቱን ማስቆም ባለመቻሉ ብቻ ሳይሆን እንዲጀመር በመርዳት ተጠያቂ ነው" ብለዋል፡፡

በተጨማሪም ትራምፕ የዩክሬኑን መሪ ከሞስኮ ጋር ሰላም መፈለግ ባለመቻላቸው ወቅሰው፤ ዩክሬን የሰላም ስምምነት ለማድረግ የተወሰነ መሬቷን ለሩሲያ አሳልፋ ልትሰጥ እንደምትችል ጠቁመዋል፡፡ ይህም የትራምፕ ንግግር በህዳር አምስቱ ምርጫ የሚያሸንፉ ከሆነ ፖሊሲያቸው ወደ ሩሲያ ሊያደላ እንደሚችል ማሳያ ነው ሲል ዘግቧል፡፡

የዘንድሮው ምርጫ ዴሞክራቶችን ከነጩ ቤት አስወጥቶ ሪፐብሊካንን የሚያስገባ ከሆነ ለዩክሬን የሚደረገው ድጋፍ በእጅጉ ሊቀንስ እንደሚችል ተነግሯል፡፡ ይህን ሃሳብ ተቀናቃኛቸው የዴሞክራት እጩ ካማላ ሃሪስም በተደጋጋሚ ሲያንጸባርቁት ከዚህ ቀደም ተስተውለዋል፡፡

"ትራምፕ አምባገነኖችን ለማወገዝ የሚግደረደር ከፑቲንም ጋር የጠበቀ ወዳጅነት ያለው ነው" ያሉት ሃሪስ፤ የፕሬዚዳንትነት ቦታውን የሚይዝ ከሆነ ዩክሬን ብቻዋን ልትቆም ትችላለች ሲሉ ተደምጠዋል፡፡ ሆኖም የሪፐብሊካኑ እጩ "ይህ ማለት በምርጫው ካሸነፍኩ ዘለንስኪን መደገፍ አቆማለሁ ማለት አይደለም፤ ምክንያቱም የሀገሪቱ ዜጎች ያሳዝኑኛል ነገር መጀመርያም ቢሆን ከሩሲያ ጋር ጦርነት እንዳይጀመር ማስቆም ነበረበት" ነው ያሉት፡፡

ባሳለፍነው መስከረም ወር ዘለንስኪ "የድል እቅድ" ያሉትን በሩስያ ላይ ተጨማሪ ጫናዎች እንዲደረጉ እና ለዩክሬን የሚደረጉ የጦር መሳሪያ ድጋፎች የረጅም ርቀት ሚሳይሎችን በብዛት እንዲያካትት የሚጠይቀውን እቅድ ለአሜሪካ መሪዎች ባቀረቡበት ወቅት ሁለቱንም ፕሬዚዳንታዊ እጩዎች "ጨዋዎች" ሲሉ ገልጸዋቸዋል።

ዶናልድ ትራምፕ በምን አይነት መንገድ እንደሆነ ግልጽ ባያደርጉም ፕሬዚዳንት የሚሆኑ ከሆነ የዩክሬን እና ሩሲያ ጦርነትን በፍጥነት እንደሚያስቆሙ በተደጋጋሚ ሲናገሩ መሰማታቸውን አል ዐይን ዘግቧል፡፡

# ስፖርት





# ተወዳጁን ስፖርት የምታሾረው ድምፅ

ቦጋለ አበበ

ከዓለም እስከ አህጉር፣ ከአህጉር እስከ ሀገር፣ ከሀገር እስከ ማህበረሰብ ብሎም እስከ ግለሰብ፣ ከትልቅ እስከ ትንሽ በእግር ኳስ ልቡ ያልተሳበና ለእግር ኳስ ፍቅር ያልተንበረከከ የለም። በርካቶች «በማራኪነቱ፤ በልብ ሰቃይነቱ፤ በአስፈንዳቂነቱም ሆነ በአሳዛኝነቱ ወደር አይገኝለትም» ሲሉ የሚመሰክሩለት እግር ኳስ፤ በዓለም አቀፍ ደረጃ እጅጉን ተቀባይ የሰላምና የፍቅር ስፖርት መሆኑንም ሳያቅማሙ ይስማሙበታል።

እንደ ሌሎች የስፖርት አይነቶች ሁሉ ተወዳጁ እግር ኳስም በዳኞች ውሳኔ ላይ እምነት ያሳደረና ውሳኔያቸውም ከበሬታና ሙሉ ሥልጣን የተሰጠው ነው። ዳኝነት በጣም ከባድ ሙያና ከባድ ሃላፊነት ይጠይቃል። ለስፖርቱ ሳቢነት፣ ማራኪነት ተወዳጅነት፤ እንዲሁም በጨዋታ ለሚገኘው ውጤት የዳኞች ጨዋታን የመምራትና የውሳኔ አሰጣጥ ብቃት እጅግ ወሳኝ ነው። ዳኞች በቅፅበታዊ ውሳኔና ፍርድ እግር ኳስን ሊገድሏትም ሆነ ሕይወት ሊዘሩባት ይችላሉ።

ለተወዳጁ ስፖርት እንደ ወይን እየጣፈጠ ዓመታትን መቀጠልም የዳኞች ሚና በቀላሉ የሚገለፅ አይደለም። አፍቃሪ እግር ኳሶችም በሜዳው ላይ ፍልሚያ ቀልባቸው የሚሳበው፤ በስፖርቱ ፍቅር የሚንበረከኩት አሊያም የሚዝናኑት፤ በማይታመኑ፣ በማይጠበቁ ልብ ሰቃይ፤ አስፈንዳቂና አሳዛኝ ክስተቶች ውጤቶች ብቻ አይደለም። በዳኞች ውሳኔ አሰጣጥ ጭምር ነው።

ቀደም ባሉት ዘመናት የጨዋታ ሕግ ማስከበሪያ መሣሪያ ባለመኖሩ ዳኞች የሜዳ ላይ ክስተቶችና በጨዋታው መሃል የሚፈጠሩ ክስተቶችን ተመርኩዘው ውሳኔ የሚሰጡት አስገራሚ በሆነ መልኩ ነበር። ጥንት የእግር ኳስ ውድድር ሲደረግ ዳኞች አማካይ የሆነ ቦታ ተፈልጎላቸው በትሪቡን መሐል ተቀምጠው ይዳኙ ነበር። ይሁንና በዚህ ዓይነት ጨዋታን መምራት ጥፋቶች ለመመልከትና ለመቆጣጠር ምቹት የሚሠጥ አይደለም በመባሉ ዳኞች ሜዳ ገብተው ጨዋታን እንዲመሩ ተደርጓል።

በዘመኑም ዳኞች ውድድሮችን የሚመሩት በፊሽካ በመጠቀም ሳይሆን በማጨብጨብ፣ በመጮህና ጨዋታውን አስቁመው በመጣራት ሲሆን፤ ይህ ዓይነቱ ዳኝነትም አስቸጋሪና አድካሚ በመሆኑ ተለውጦ ቃጭል ወይም ትንሽ ደውል በማንቃጨል ጨዋታውን መምራት እንደ አማራጭ ሆኖ ቀርቧል። ይህን አማራጭ በመከተል ዳኞች ጨዋታን በመምራት ሂደት ጥፋትን ጨምሮ ሌሎችን ውሳኔዎችን ለማሳለፍ እየተሯሯጡ በትንሽ ደውል ቃጭል ቢያንቃጭሉም ሰሚ ግን አልነበራቸውም።

ይሁንና በ19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ እንግሊዛዊው ጆሴፍ ሁድሰን ፊሽካን ለዓለም ማስተዋወቁን ተከተሎ በትንሽ ደውል ቃጭል እያንቃጨሉ እግር ኳስን የመምራት ታሪክ ተቋጨ።



በእርግጥ ቀደም ባሉት ዓመታት ዘመናዊም ባይሆን ፊሽካዎች መኖራቸው አይካድም።

ይሁንና የፊሽካ ግልጋሎት በተለይ ከጥንታዊው የግሪክ ሥልጣኔ ጀምሮ የዘውድ ቤተመንግሥት ወይንም ከተማ ጠባቂዎች ድንገተኛ ጠላት በሚታያቸው ወቅት ሠራዊትና ሕዝቡን ለማንቃት፤ ለማስጠንቀቅ ብሎም ለማስታጠቅ ይጠቀሙበት እንጂ የእግር ኳስን ሕግ ለማስከበር ጥቅም ላይ አልዋለም።

ምስጋና «የፊሽካው ፈጣሪ» የሚል ስያሜን ላገኘው ጆሴፍ ሁድሰን ይሁንና ፊሽካ በእንግሊዝ ሀገር በርሚንግሃም የእግር ኳስ ዳኞች የጨዋታ ሕግ ማስከበሪያ መሣሪያ ለመሆን በቅቷል። ለመጀመሪያ ጊዜ እግርኳስ ጨዋታን ለመምራት ጥቅም ላይ የዋለውም እኤአ 1878 /79 የውድድር ዓመት በተካሄደው በፉትቦል አሶሴሽን ካፕ በኖቲንግሃም ፎረስት እና በሼፊልድ ክለቦች ጨዋታ ስለመሆኑ የታሪክ ድርሳናት ያስረዳሉ።

የእግር ኳስን ሕግ ለማስከበር ጥቅም ላይ ከዋለው ፊሽካ የምትወጣው ይህች ድምፅ አስደንጋጭም፣ አስደሳችም አሳዛኝም ናት። በርካቶችን ልባቸው ቀጥ እስኪል ባሉበት እንዲቀሩ ምክንያት ሆናለች። አንዳንዶችን በድንጋጤ አድርቃ እስከ ወዲያኛው ላይመለሱ ሸኝታለች። ይህች ድምፅ ጥቂት የማይባሉትን ደግሞ በሕይወት ዘመን አንዴ ከሚከሰትና ከማይደገም ጮቤ ጋር ውላ አሳድራለች።

በአሁኑ ወቅት ግልጋሎት በመስጠት ላይ የሚገኙት የፊሽካ አይነት ዲዛይኖች ይፋ የሆኑት እኤአ 1884 በጆሴፍ ሁድሰን አማካኝነት ነው። ቀደም ሲል ከተሠራው በድምፅም ሆነ በጥራት ዘመናዊ የሆነውን ይህን ፊሽካም ዜግነቱ የኒውዝላንድ የሆነው ዊሊያም አታክ የተባለ ግለሰብ እኤአ 1884 በተካሄደ በራግቢ ጨዋታ ላይ ተጠቅሞታል።

ይህም ግለሰብ ዘመናዊውን የእግር ኳስ ፊሽካ በመጠቀም ስፖርታዊ ጨዋታን በመምራት በታሪክ የመጀመሪያው ዳኛ አድርጎታል። በአሁኑ ወቅት ትንሽየዋ ክብ መሳይ ከብረት፤ ከፕላስቲክ አሊያም ከእንጨት የምትሠራው ፊሽካ በማምረት Fox 40 የተባለን ድርጅት የሚስተካከሉት ይቆጠሩ ቢባል ከአንድ እጅ ጣት አይበልጡም።